# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 245 ግንቦት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ጽዱ ከተማ ለመፍጠርና የጽዳት ባህላችንን ለመቀየር በትብብር እንሥራ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አሳሰቡ

## - በዲጂታል ቴሌቶኑ ከ154 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ጽዱ ከተማ ለመፍጠርና የጽዳት ባህላችንን ለመቀየር በትብብር እንሥራለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ። ዲጅታል ቴሌቶኑ በአጠቃላይ 154 ሚሊዮን 500 ሺህ ተሠብስቧል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የጽዱ ኢትዮጵያ የአንድ ጀንበር የ50 ሚሊዮን ብር ዲጂታል ንቅናቄን አስመልክቶ ትናንት በተዘጋጀ መድረክ ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል።

በወቅቱ በመዲናችን በርከት ያሉ መጸዳጃ ቤቶች በትብብር መንፈስ በጋራ ብንሠራ ከዚያ ቀጥሎ ሆቴሎችና ቢሮዎች እንዲሁም የንግድ ቤቶች መጸዳጃ ቤቶቻቸውን የማይዘጉ ከሆነ ጽዱ ከባቢና ከተማ መፍጠር እንችላለን ሲሉ ገልጸዋል።

ለጽዱ ኢትዮጵያ ድጋፍ ያደረጉ የታክሲ ማህበራት በተገኙበት ሕዝቡን በማገልገል ደረጃ ከፍተኛ ሥራ እየሠሩ መሆናቸውን አንስተው፤ በአዲስ አበባ የታሪፍ ጭማሪ እንዳይደረግ ክልከላ ሲደረግ በትብብር የሚሠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የታክሲ ማህበራት የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት መፀጸዳጃ ቤቶች ያስፈልጋቸዋል። ለዚህም ለሕዝብ የሚሆኑ መፀዳጃ ቤቶችን እየሠራን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የታክሲ ማህበራት ለጽዱ ኢትዮጵያ ድጋፍ በማድረጋቸው ጠቅላይ


ጽዱ ከተማ ለመፍጠርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










## ስለአምራች ኢንዱስትሪው ውጤታማነት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ ይገባል

- ለጥናትና ምርምር እየወጣ ያለው ገንዘብ ዜሮ ነጥብ 27 ብቻ ነው


ገጽ 4




## በኢትዮጵያ

## ከአንድ ሺህ 500 በላይ የሙስና ጥቆማዎች ቀርበዋል


ገጽ 4


# በትርክት በሚገነባ የአብሮነት ድልድይ የሕዝብ አንድነትን የሚያረጋግጡ ሥራዎች ይሠራሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በድንጋይና በሲሚንቶ በሚሠራ ድልድይ ብቻ ሳይሆን በትርክት በሚገነባ የአብሮነት ድልድይ የሕዝባችንን አንድነት እናረጋግጣለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በታላቁ ወንዝ የተገነባውን ታላቁን ድልድይ ትናንት መርቀው ሥራ አስጀምረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፤ እኛ ሁለት ድልድይ መገንባት እንፈልጋለን ብለው፤ የሕዝባችንን አንድነት እናረጋግጣለን የምንለው በድንጋይ እና በሲሚንቶ የሚሠራ ድልድይ ብቻ ሳይሆን በትርክት በሚገነባ የአብሮነት ድልድይም ጭምር ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ድልድዩ ወገን ከወገን፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያገናኝ ንግድ የሚያሳልጥ በሰዎች አዕምሮ


በትርክት በሚገነባ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ዶክተር ጉሻ በለኮ

## በክልሉ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከስምንት ሺህ በላይ ሰዎች በኤች. አይ.ቪ ቫይረስ ተይዘዋል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከስምንት ሺህ በላይ ሰዎች በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ መያዛቸውን የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የኤች. አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዘርፍ ኃላፊ ዶክተር ጉሻ በለኮ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ የስርጭት መጠንን ለመቀነስና ለመቆጣጠር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለሁለት ሚሊዮን 519 ሺህ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ምርመራ ማድረግ ተችሏል።

ከተመረመሩት ውስጥ ስምንት ሺህ 097 ያህል ሰዎች በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው የተገኘ መሆኑን አስታውቀው፤ ቫይረሱ በደማቸው ከተገኘባቸው ሰዎች ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት መድኃኒት የጀመሩ መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ በዘጠኝ ወራት የታየው የቫይረሱ የሥርጭት መጠን ዜሮ ነጥብ 32 በመቶ ነው ያሉት ዶክተር ጉሻ፤ የሥርጭት መጠኑ ካለፈው ዓመት ከነበረው ዜሮ ነጥብ አራት በመቶ የሥርጭት መጠን ቅናሽ አሳይቷል ብለዋል።

ዶክተር ጉሻ እንደገለፁት፤ በኦሮሚያ ክልል ደረጃ እስካሁን ባለው ሂደት በአጠቃላይ 132 ሺህ 164 የሚሆኑት ዜጎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ በምርመራ ተረጋግጧል። አጠቃላይ በቫይረሱ ከተያዙት ሰዎች ውስጥም 129 ሺህ 153 የሚሆኑት መድኃኒት ተጠቃሚ ናቸው።

የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 104 ሺህ ሰዎች ላይ በተደረገ የቫይረስ መጠን ምርመራ 101 ሺህ የሚሆኑት በደማቸው ያለው የቫይረስ መጠን በሚፈለገው ልክ ዝቅ ማድረግ መቻሉንም አብራርተዋል።

በአጠቃላይ ኦሮሚያ ክልል ያለው የስርጭት ምጣኔ ዜሮ ነጥብ ስድስት በመቶ ሲሆን እንደ አዳማ፣ ሻሸመኔ እና ቢሾፍቱ ያሉ ከተማዎች ላይ የስርጭት ምጣኔው እስከ ሦስት በመቶ ከፍ ይላል።

ከ18 እስከ 28 ዓመት በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች፣ ሆቴል አካባቢ የሚሠሩ ሠራተኞች፣ ማረሚያ ቤት እና ሹፌሮች ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸውንም ኃላፊው አስታውቀዋል።

ያታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች በ72 ሰዓት ውስጥ ወደ ጤና ተቋም በመምጣት በሽታውን ቅድሚያ ለመከላከልና መድኃኒቶች ሳያቋርጡ በአግባቡ መከታተል አለባቸው ብለዋል።

በክልሉ የመድኃኒት አቅርቦት የተወሰነ መቆራረጥ ቢኖርም በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያሉ ሲሆን፤ በማህረሰቡ ዘንድ በሽታው የለም የሚል የተሳሳተ እሳቤን በኩል ግንዛቤ የመስጠት፣ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት እንዲሁም በሽታው በደማቸው ላሉ የመድኃኒት አገልግሎት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ዶክተር ጉሻ ተናግረዋል።

ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎች የረጅም ጊዜ ገቢ ማስገኛ ተግባራት በትኩረት የሚሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ማህበረሰቡ ስለበሽታው አስጊነት ተረድቶ እራሱን ከበሽታው መከላከል ይኖርበታል ሲሉ ዶክተር ጉሻ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን ተችሏል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት በመንግሥትና በማህበረሰቡ ያልተሸፈኑ የልማት ሥራዎችን በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በመከወን ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን መቻሉን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሴክተር እቅድ አፈጻጸሙን ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤር አቅርቧል።

በወቅቱ ሪፖርቱን ያቀረቡት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በክረምትና በበጋ ወራት የወጣቶችን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሀ ግብሮች በ13 የስምሪት መስኮች ሲሠራ ቆይቷል።

ስምሪቶቹ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፣ አቅመ ደካሞችን ቤት መገንባትና ማደስ፣ በደም ልገሳ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎትና በሰብዓዊ ድጋፎች መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር 24 ሚሊዮን 599 ሺህ አንድ መቶ ወጣቶችን ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።





በተጨማሪም በወሰን ተሻጋሪ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ በሚል መሪ ሃሳብ ከሁሉም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የተውጣጡ ወጣቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በመዘዋወር አገልግሎቱን እንዲሰጡ ተደርጓል ብለዋል። ይህም የበጎ ፈቃደኝነት ግንዛቤ በወጣቶች እንዲዳብር ከማድረጉ ባለፈ የማህበረሰቡ ትስስር እንዲጎለብት፣ ወጣቱ የማህበረሰቡን እሴቶች፣ ልምዶችና ባህሎች እንዲቀስም ዕድል የፈጠረ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በመንግሥትና በማህበረሰቡ ያልተሸፈኑ የልማት ሥራዎችና ማህበራዊ አገልግሎቶች በወጣቶች በመከወን 18 ቢሊዮን 577 ሚሊዮን 399 ሺህ 521 ብር የሚገመት ሀብት ማዳን ተችሏል። በዚህም 58 ሚሊዮን 199 ሺህ 518 የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት መደበኛ ባልሆነ ፍልሰት ወደ ተለያዩ ሀገራት ሄደው የሚመለሱ ተጎጂዎችን በመቀበል የሥነ-ልቦናና የማህበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ሰፊ ሥራ ሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል። በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከተለያዩ ሀገራት 58 ሺህ 210 ዜጎች ወደ ሀገር ገብተው የሥነ ልቦናና ማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ 47 ሺህ 746 ዜጎች በሱዳን የእርስ በእርስ ግጭት ምክንያት ወደ ሀገር የገቡ ሲሆን ከሳውዲ ሰባት ሺህ 236፣ ከየመን ሁለት ሺህ 474 ዜጎች እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት ወደ ሀገር መግባታቸውን ተናግረዋል።

ከተመለሱት ዜጎች 29 ሺህ 464 ወንዶች ፣ 27 ሺህ 996 ሴቶች እንዲሁም 750 ህጻናት መሆናቸውን አክለዋል።

# ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ በሽታን የሚቋቋሙ 20 አዳዲስ የሰብል ዝርያዎችን እያስተዋወቀ ነው

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- በየዓመቱ በሽታን የሚቋቋሙና በፍጥነት የሚደርሱ 20 አዳዲስ የሰብል ዝርያዎች ለአርሶ አደሮች እያስተዋወቀ መሆኑን የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተርና ተመራማሪ ተሾመ ቦጋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምርምር ተቋሙ ያሻሻላቸውን የሰብል ዝርያዎችን የማባዛትና የማስተዋወቅ ሥራዎችን በትኩረት እየሠራ ይገኛል።

በኢንስቲትዩቱ በስፋት የሚካሄደው ምርምር የምግብ ሰብል ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ በየዓመቱ 20 የሚደርሱ በሽታን የሚቋቋሙና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደርሱ አዳዲስ የሰብል ዝርያዎች ይተዋወቃሉ ብለዋል።

በአሁኑ ወቅትም ኢንስቲትዩቱ የተሻሻሉ የስንዴ፣ የገብስ፣ የበቆሎ፣ የማሽላ፣ የጤፍ እንዲሁም የሩዝ ዝርያዎችን በማውጣት ከውጭ ይገቡ የነበሩ ዝርያዎችን እየተካ ለገበሬው በማስተዋወቅ ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

ማሽላና ጤፍ ከዚህ ቀደም ዝናባማ አካባቢዎች ላይ የሚመረቱ የነበረ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ብዙ ውሃ የማይፈልጉና ዝናብ አጠር አካባቢዎች መመረት የሚችሉ የጤፍና የማሽላ ዝርያዎችን በማስተዋወቅ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ ተሾመ እንዳመለከቱት፤ ሀገሪቱ ወደ ውጭ ከምትልከው አንዱ በሆነው የሀረርጌ ቡና ላይ ስድስት የቡና ዝርያዎች ወጥተው ለገበሬው በመተዋወቅ ላይ ይገኛሉ። በምርምር እየተገኙ ያሉ ዝርዎች በምግብ እራስን ከመቻል ባለፈ የውጭ ምንዛሬም ለማግኘት ይረዳሉ።

የውጭ ምንዛሬን ከሚያስገኙ ምርቶች መካከል የሰሊጥ፣ የቦሎቄና ማሾ ዝርያዎችን በማሻሻል እንዲሁም የተለያዩ የአመራረት ዘዴዎችን በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ እይተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የፍራፍሬ ዝርዎች ላይ ምርምር እያካሄደ መሆኑን ጠቁመው፤ አቮካዶና ሙዝ ላይ በተሠራ ምርምር ሰባት የሙዝ ዝርያዎች ለገበሬው መተዋወቃቸውን ገልጸዋል።





አቶ ተሾመ ምርትና ምርታማነት ቀጣይነት እንዲኖረው የሰብል ዝርያን ከማሻሻል በተጨማሪ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ላይ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ኢንስቲትዩቱ በስፋት እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

አፈር እንዳይጎዳ የሚጠቅሙ ተመጣጣኝ ዘር አጠቃቀም፣ የማዳበሪያና የውሃ አመጣጠንን በተመለከተ ተማራማሪዎች እንዲሁም የግብርና ባለሙያዎች ለገበሬው እንዲያስተምሩ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ዳይከተሩ እንዳስታወቁት፤ በኢንስቲትዩቱ የግብርናው ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን በርካታ ምርምሮች እየተሠሩ ቢሆንም ካለው ሀገራዊ ችግር አንጻር ሰፊ ሥራ በቀጣይም ይጠበቃል።



ዶክተር ይታያል አዲስ

## ምርቱ እስከ 290 ሚሊዮን ዶላር ገቢ የሚያስገኘውን **«ማካዳሚያ ነት»** ዛፍ በኢትዮጵያ ማልማት ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ምርቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ109 ሚሊዮን እስከ 290 ሚሊዮን ዶላር ገቢ የሚያስገኘውን "ማካዳሚያ ነት" ዛፍ በስፋት በኢትዮጵያ ማምረት እንደሚገባ የአካባቢ ጤና እና ተፈጥሮ ሀብት ማህበር ገለጸ።

የአካባቢ ጤና እና ተፈጥሮ ሀብት ማህበር ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ይታያል አዲስ እንደገለጹት፤ ማካዳሚያ ነት ዛፍ ከአራት እስከ አምስት ዓመት ውስጥ ምርት መስጠት በመጀመር ለአንድ መቶ ዓመት ምርት ያለማቋረጥ መስጠት የሚችል ነው።

የማካዳሚያ ነት ዛፍ የሚሰጠው ምርትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬን ለማግኘት እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ አጠባበቅ ጉልህ ሚና እንዳለው አስታውቀው፤ ምርቱ በኪሎ ግራም 21 ዶላር የሚያወጣ መሆኑንም ዶክተር ይታያል ገልጸዋል።

ደቡብ አፍሪካ ምርቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ290 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንዲሁም ኬንያ 109 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘታቸውን በማሳያነት ጠቅሰዋል።

ዛፉ ከ15 ዓመት በታች ከ25 እስከ 28 ኪሎ ግራም እንዲሁም ከ15 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ዛፍ ከ80 ኪሎ ግራም በላይ ምርት መስጠት ይችላል ያሉት ዶክተር ይታያል፤ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጤናማ ቅባቶችን፣ ቫይታሚን እና ማዕድናት ያካተተ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አላስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ለማስወገድ፣ የደም ካንሰርን የሚቀንስ፣ ክብደትን የሚያስተካክልና የልብ ህመምን ለመከላከል የሚረዳ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በተጨማሪም "ማካዳሚያ ነት " ከሚሰጠው የምርት ጥቅም ባሻገር እንደ ቡና፣ ሻይ ቅጠል፣ በቆሎና ሌሎች የእፅዋት ዝርያዎች ከጸሀይ በመከላከል ምርትን ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ያሉት ዶክተር ይታያል፤ የደን ሽፋንን ለማሳደግ እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ያስችላል ብለዋል።

እሴቶችን በመጨመር በቅቤነት፣ ወተት፣ ኬክ እና ለምግብ ዘይትነት መስሪያነት የሚያገለግል እንዲሁም በማር ምርት አካባቢዎች ላይ ንቦችን ለመሳብ እንደሚረዳም አስታውቀዋል።

ማህበሩ ዛፉ ሀገር ውስጥ እዲገባ እና ምርት እንዲጀመር ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማህበሩ ለያዘው ውጥን መሳካት በአካባቢ ጥበቃና ሥነምህዳር እንዲሁም አየር ንብረት ለውጥና ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ የተሠማሩ የመንግሥትም ሆነ የግል አካል አካላት ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

"ማካዳሚያ ነት" ዛፍ መነሻውን በአውስትራሊያ ያደረገ ሲሆን በሌሎች እጽዋት ላይ ምንም ጉዳት የማያደርስ እና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዳ ነው።

# በክልሉ ከ319 ሺህ በላይ ዜጎች በንግድ ዘርፍ የሥራ ዕድል አግኝተዋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ319 ሺህ 533 ሰዎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የክልሉ ንግድ ቢሮ አሳወቀ። በተደረገ ቁጥጥር ከ150 ሺህ በላይ የንግድ ድርጅቶች ሕገ ወጥ ሆነው መገኘታቸውም ተመላክቷል።

የቢሮው የእቅድና በጀት ግምገማ ዳይሬክተር ዲናኦል ደረጄ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቢሮው በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በቋሚና ጊዜያዊነት ባጠቃላይ 337 ሺህ 401 የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅዶ ለ319 ሺህ 533 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።





በሸቀጣሸቀጥ፣ በኢንዱስትሪ ምርቶች ንግድ፣ በግብርና ምርቶች ንግድና በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ገቢ ማግኘት መጀመራቸውንም ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 150 ሺህ 680 አዲስ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 113 ሺህ 236ቱን በማከናወን የዕቅዱን 75 በመቶ መፈጸም ተችሏል ብለዋል።

አፈጻጸሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ21 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን ተናግረዋል።

በዘጠኝ ወራት ውስጥ 596 ሺህ 511 የንግድ ፍቃዶችን ለማደስ ታቅዶ 453 ሺህ 42ቱን ማከናወን እንደተቻለም አክለው አስረድተዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በዘጠኝ ወራት ውስጥ 871 ሺህ 983 የንግድ ድርጅቶችን መቆጣጠር የተቻለ ሲሆን፤ ሕጋዊ መስመር ይዘው እንዲሠሩ የሚያስችል ክትትል ተደርጓል።

በተደረገው ቁጥጥር 150 ሺህ 712 የንግድ ድርጅቶች ሕገ ወጥ ሆነው መገኘታቸውን አስታውቀዋል። በተደረገው ክትትል ከተለያዩ ቅጣቶች ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መደረጉንም አያይዘው አስታውቀዋል።

በተጨማሪ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ242 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት በኮንትሮባንድ ሲንቀሳቀስ መያዙንና ከንግድ አገልግሎት አሰጣጥ ከ131 ሚሊዮን ብር መገኘቱን ገልጸዋል።

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በክልሉ በዜግነት አገልግሎት የቢሮውን ሠራተኞችና መዋቅሮችንና ነጋዴዎችን በማስተባበር ከ21 ሚሊዮን ብር በላይ የተለያዩ ድጋፎች ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

በአጠቃላይ በክልሉ በዜግነት አገልግሎት 339 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ብር ማዳን እንደተቻለ ጠቁመዋል።

# ኮሌጁ ብቁ መምህራንን በማፍራት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የባህርዳር መምህራን ኮሌጅ ብቁ መምህራንን በማፍራት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየሠራ መሆኑን ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አስናቀው ታደለ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ኮሌጁ በሙሉ አቅሙ ጥራት ያለው የመምህራን ትምህርት ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል። ብቁ መምህራንን በማፍራትም የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየሠራ ነው።

ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዞ ከሚነሱ ውስንነቶች አንዱ የመምህራን ሥልጠና ነው ያሉት ዶክተር አስናቀው፤ የትምህርት ጥራትን በሚፈለገው ልክ ለማረጋገጥ ለመምህራን ሥልጠና ተገቢውን ትኩረትና ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

ዶክተር አስናቀው አክለውም፤ በኮሌጁ ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ያሉ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በየትምህርት ዓይነቱ ለ40 ተማሪዎች ሥልጠና እየሠጠ ነው ብለዋል።

በመጪዎቹ ጊዜያት በዓመት ከሶስት ሺህ በላይ ተማሪዎችን ለመቀበል አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም



አስናቀው ታደሰ ዶ/ር

አብራርተዋል።

በተጨማሪም ከተለያዩ ሀገራት የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው መምህራን በማምጣት ለአጭር ጊዜ ሥልጠና ለመስጠት ስለመታቀዱንም ነው ዶክተር አስናቀው ያነሱት።

እንደ ዶክተር አስናቀው ገለጻ፤ ከዚህ በፊት የመምህራን ትምህርርት ተበታትኖ በተለያዩ ዘርፍ ነበር የሚሰጠው። ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተሠራ ሥራ ወደ አንድ ማምጣት ተችሏል።

ተበታትነው የነበሩት ወደ አንድ መምጣታቸው በሥልጠና ሂደቱ ጥራት ያላቸውና ተደራሽ የሆኑ ሥራዎች ለማሠራት እንዲሁም የመምህርነት እሴትን ከመጀመሪያው ጀምረው እያዳበሩ እንዲሄዱ የሚያግዝ መሆኑን አብራርተዋል።

ኮሌጁ በመምህራን ሥልጠና የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበተ ነው ያሉት ዶክተር አስናቀው፤ የመምህራን ትምህርት ሥልጠና ይበልጥ ለማሻሻል እንዲቻል የሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ ምክረ- ሃሳብ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል ብለዋል።

ትምህርት ኮሌጁ እራሱን ችሎ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የመሆን ራዕይ ሰንቆ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ዶክተር አስናቀው ገልጸዋል።

በኮሌጁ ሞዴል የሆኑ የመምህራንና የትምህርት አስተዳደር ባለሙያዎች ለማብቃት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በተያዘው በጀት ዓመት በቋንቋ፣ በተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዓይነቶች መምህራንን እያሠለጠነ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ዶክተር አስናቀው፤ ኮሌጁ በሁለት ትምህርት ቤቶችና በሶስት ትምህርት ክፍል ተደራጅቶ እየተሠራ ይገኛል ያሉ ሲሆን አገልግሎትን ለማሻሻልም አዲስ ኮምፕሌክስ ህንጻ እየገነባ መሆኑም ተናግረዋል።

# ለአምራች ኢንዱስትሪው ውጤታማነት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ ይገባል

## - ለጥናትና ምርምር እየወጣ ያለው ገንዘብ ዜሮ ነጥብ 27 ብቻ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ለአምራች ኢንዱስትሪው ውጤታማነት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ ይገባል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) ገለጹ። ለጥናትና ምርምር እየወጣ ያለው ገንዘብ ዜሮ ነጥብ 27 ብቻ መሆኑም ተመላክቷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሚሊኒየም አዳራሽ በከፈቱት ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ "ጥናትና ምርምር ለተሻለ አቅም ግንባታ" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በወቅቱ የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) እንደገለጹት፣ በትምህርት ሥርዓት ማሻሻያው የትምህርት ተቋማት የእውቀት ማዕከል እንዲሆኑና የሀገሪቱን ኢኮኖሚና አምራች ኢንዱስትሪውን እንዲደግፉ እየተሠራ ነው።

እንደ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገለጻ፣ አምራች ኢንዱስትሪውን ውጤታማ ለማድረግ የትምህርት ዘርፉ የላቀ ሚና ይጠበቅበታል። ለዚህም ለትምህርት ጥራት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ሲሆን፣ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

የትምህርት ሥርዓት ማሻሻያው ከአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ከጥናትና ምርምር ጋር ትስስር እንዲኖረው እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፣ ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሩት ጥናትና ምርምር ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር ያለው እንዲሆን ግዴታ መጣሉን አስታውቀዋል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎችም ለጥናትና ምርምር በጀት መመደብ እንዳለባቸውና ተማሪዎች በተግባር የሚማሩበትን ምቹ ሁኔታን ሊፈጥሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ለጥናትና ምርምር እየወጣ ያለው ገንዘብ ዜሮ ነጥብ 27 ብቻ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በቀጣይ ለጥናትና ምርምር የሚመደበውን በጀት ማሳደግ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ሩዋንዳ ዜሮ ነጥብ ስምንት በመቶ፣ ግብጽ ደግሞ አንድ በመቶ ከጥቅል ሀገራዊ ምርታቸው ለጥናትና ምርምር እንደሚያወጡ ገልጸው፣ ኢትዮጵያም ለጥናትና ምርምር የምታወጣው ገንዘብ በአማካኝ ወደ ሁለት በመቶ ከፍ ማለት እንዳለበት አስታውቀዋል፡፡



ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)



አቶ መላኩ አለበል

ከዚህ በፊት አምራች ኢንዱስትሪዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ለጥናትና ምርምር የሚመድቡት ገንዘብ አለመኖሩን ገልጸው፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን መንግሥት፣ የግሉ ሴክተርና ባለድርሻ አካላት እገዛ ማድረግ አለባቸው ብለዋል፡፡

በቀጣይ የሚመደበውን ገንዘብ በመጨመር አምራች ኢንዱስትሪውን በፖሊሲና በጥናትና ምርምር መደገፍ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ኢንዱስትሪውን ለማገዝና በእውቀት የዳበረ የሰው ኃይል ለማፍራት የትምህርት ሥርዓት ማሻሻያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፣ ከታችኛው የክፍል ደረጃ ጀምሮ የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ ተማሪዎች የተማሩትን ተግባር ላይ የሚያውሉ እና የማህበረሰቡን የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የሚቀይር እውቀት እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በበኩላቸው፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም ለማሳደግና ተወዳዳሪ ለማድረግ በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅምና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በአቅም ግንባታ፣ በጥናትና ምርምር መደገፍ እንደሚገባ ገልጸው፣ ለዚህም ከትምህርት ተቋማትና በዘርፉ ከሚሠሩ ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራቱ የግድ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መላኩ ከሆነ፣ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ምርትን በሀገር ውስጥ መተካት ትኩረት ተሰጥቶታል፡ ፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የትምህርት ተቋማት የተማሪዎችን ዩኒፎርም፣ ጫማና ቦርሳ የሀገር ውስጥ ምርትን በመጠቀም ዓርዓያ ሊሆኑ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ በቴክኒክና ሙያ የሚያልፉ ዜጎች ክህሎት መማርና በገበያው ተፈላጊ የሆነ ሥልጠናን እንዲያገኙ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የሰው ኃይል የማፍራት ሥራ በልዩ ትኩረት እየተሠራ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

# በኢትዮጵያ ከአንድ ሺህ 500 በላይ የሙስና ጥቆማዎች ቀርበዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከአንድ ሺህ 500 በላይ ሙስናን የተመለከቱ ጥቆማዎች መቅረባቸውን የፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በኮሚሽኑ የሙስና መረጃ አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ፈርዳ ገመዳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኮሚሽኑ ከፌዴራል ተቋማት እንዲሁም ከክልሎች ሙስና ነክ የሆኑ ጥቆማዎችን እየተቀበለ ይገኛል።

በ2016 በጀት ዓመት እስካሁን ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አንድ ሺህ 451 ሙስናን የተመለከቱ ጥቆማዎች መቅረባቸውን አቶ ፈርዳ ተናግረዋል።

ለክልል የሚደርሱ የሙስና ጉዳዮች ወደ ኮሚሽኑ ሳይደርሱ ከክልሉ የሕግ አካላት ጋር በመሆን እንዲመረመሩ ይደረጋል ያሉት አቶ ፈርዳ፣ ከፌዴራል ተቋማት በቀጥታ ለኮሚሽኑ ከደረሱት 80 የሙስናን ጥቆማዎች መካከል 65ቱን ጥቆማዎችና መረጃዎቹን ለፌዴራል ፖሊስ አሳልፎ በመስጠት የማጣራት ሥራዎች መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

ወደ ኮሚሽኑ መረጃ ክፍል ከሙስና ጥቆማዎች በተጨማሪ የተለያዩ የመልካም አስተዳደርና ሌሎች ቅሬታዎች እንደሚመጡ ጠቁመው፣ በዚህም ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 265 ቅሬታዎችን ተቀብሎ ጉዳዩ ወደሚመለከታቸው አካላት መምራቱን አስረድተዋል።

ወደ ኮሚሽኑ የሚመጡ ጥቆማዎች ሁሉም የተረጋገጡ የሙስና ወንጀሎች ናቸው ማለት እንደማይቻልና አንዳንዶች ያለምንም ማስረጃ የግል ፀብን በመያዝ የሚቀርቡም ይኖራሉ ብለዋል፡፡

አንዳንድ ጥቆማዎችን መሠረት አድርጎ ጉዳዮች ሲመረመሩ ምንም አይነት ማስረጃ የማይገኝበት ከሆነ በሥራችን ላይ ጊዜ ያባክናል በመሆኑም የተረጋገጠ መረጃን ይዞ ጥቆማ ማቅረብ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ችግሩም የሙስና መከላከል ርምጃን ወደ ፊት ለማራመድና ተጠያቂነትን ለማስፈን አስቸጋሪ ሁኔታን እየፈጠረ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች የኮሚሽኑን የሥራ ኃላፊነት በአግባቡ ካለመገንዘብ የተነሳ ኮሚሽኑ የማይፈታቸውን የተለያዩ ቅሬታዎችን ይዘው የሚመጡበት ሁኔታ ሌላኛው የኮሚሽኑ ሥራ ላይ ችግር እየፈጠረ የሚገኝ ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል፡፡

አቶ ፈርዳ እንዳመለከቱት፣ በሀገሪቱ የሙስና ፈጻሚዎች ጉዳይ አሁንም አሳሳቢ መሆኑን በየጊዜው እየተሠሩ ያሉ ጥናቶች ስለሚጠቁሙ ህብረተሰቡ ከሙስና ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለመስጠት ያለው ተባባሪነት ሊጠናከር ይገባል።

ሙስና ሀገርን የሚጎዳ ጸያፍ ተግባር መሆኑን በመረዳት ሁሉም ዜጋ ለሕገወጥ ድርጊቱ ተባባሪ ባለመሆንና ሙስና ፈጻሚዎችን ለይቶ በማውጣት ተሳትፎውን ማሳደግ እንዳለበት አመላክተዋል።

# ጽዱ ከተማ ለመፍጠርና ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሚኒስትር ዐቢይ ምስጋና አቅርበውላቸዋል።

ከተማችንን ካጸዳን በኋላ ደግሞ ታክሲዎቻችንን በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ በመቀየር አካባቢያችንን ጽዱ የማድረጉ ሥራ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጀማል አሕመድ በበኩላቸው፣ ውጭ ሀገራት ስንሄድ የሚያነሱብንን የአካባቢ ጽዳት ችግር የመቅረፍ ኃላፊነቱ የእኛው ነው ብለዋል።

ሚድሮክ አዲስ አበባን ጽዱና ውብ ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት በገንዘብ እየደገፈ መሆኑን ተናግረው፣ ለጽዱ ኢትዮጵያ በግላቸው የአንድ ሚሊዮን ብር በአጠቃላይ ድርጅቶቹ ደግሞ የ50 ሚሊዮን ብር እንዲሁም ሠራተኞቹ 13 ሚሊዮን ድጋፍ ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

የውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ባለቤትና ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ዳዊት ኃይሉም በበኩላቸው፣ ጽዱ ኢትዮጵያን መደገፍ የጤና ሥርዓታችንን ለማሻሻል ወሳኝነት አለው ሲሉ ተናግረዋል።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል የሚያስችል መሠረታዊ ጉዳይ ነው ያሉት አቶ ዳዊት፣ በተለያዩ ቦታዎች ንጽህናን መጠበቅ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን በጋራ መገንባት ይኖርብናል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ከክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች ጋር በመሆን ከአራት ዓመት ተኩል በፊት ግንባታው የተጀመረውን የዓባይ ድልድይ ትናንት መርቀዋል።

ይህ ዘመናዊ ድልድይ የ380 ሜትር ርዝመት እና 43 ሜትር ስፋት ያለው በሁለቱም የመንገድ ክፍል ባለሶስት መስመር የተሽከርካሪ መንገድን ብሎም በጎን የብስክሌት መጋለቢያ መስመር የተሰናዳለት ግዙፍ ድልድይ ነው።

በጽዱ ኢትዮጵያ ዲጅታል ቴሌቶን በአንድ ጀንበር ሃምሳ ሚሊየን ለማሰባሰብ ታቅዶ ዛሬ ጠዋት በተጀመረው መርሀ ግብር 67 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ተሠብስቧል።

ንግድ ባንክ በገባው ቃል መሠረት ያስገባው 23 ሚሊዮን ሲደመር 90 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ሲሆን ሜድሮክ ካስገባው 64 ሚሊየን ጋር 154 ሚሊዮን 500 ሺህ ብር ተሠብስቧል። አጠቃላይም 40 ሺ 533 ተሳታፊ ሆነዋል።

የባህርዳር ከተማ ታላቅ መለያ ምልክት እንዲሆን የተገነባው የዓባይ ወንዝ ድልድይ የአካባቢውን የኢኮኖሚ እድገት ብሎም የመገናኛ አውታር የሚያነቃቃ ይሆናል ተብሏል።

# በትርክት በሚገነባ የአብሮነት ድልድይ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የታሰበ፣ ገንዘብ እና ጉልበት ዕውቀት የፈሰሰበት ነው ብለዋል።

"ኢትዮጵያ የሚገባትን፣ የአማራ ሕዝብ የሚገባውን፣ ለባሕር ዳርም ውበት የሚመጥን ታላቁን ሥራ በጋራ ለማስመረቅ በቅተናል" ሲሉ ተናግረዋል።

በሕዝቦች መካከል በነበሩ አልባሌ ትርክቶች ምክንያት እየላላ ያለውን ትስስር ሊያጠናክር የሚችል የትርክት ድልድይ መገንባት እንፈልጋለን ነው ያሉት። ውቡ እና ትልቁ ድልድይ እኛነታችንን፣ ፍላጎታችንን፣ መሻታችንን ያሳያል ብለዋል።

በተደጋጋሚ ለኢትዮጵያ ብልጽግናን እንመኛለን ስንል በንግግር ያልተገነዘቡን ሰዎች በዚህ ድልድይ ብልጽግና ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲረዱ እፈልጋለሁ ነው ያሉት።

ብልጽግና ለዛሬ ሳይሆን ለትውልድ የሚሠራ፣ በኢትዮጵያ ልክ ትልቅ አድርጎ የሚሠራ፣ ለሕዝቡ የገባውን ቃልና በተግባር ያስጀመረውን በማስጨረስ የሚያረጋግጥ ነውም ብለዋል።

ታላቁ የአማራ ሕዝብ በጥልቀቱ ልክ ራሱን አልምቶ፣ ራሱን አሻሽሎ ከችግር የወጣ እንዲሆን ትብብር እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል። እኛ ለዚህ ትልቅ ሕዝብ ያለን መሻት እና ፍላጎት አንድነቱን፣ ሰላሙን ጠብቆ፣ ልማቱን ማረጋገጥ እንዲችል ነው ብለዋል።

በጫካ ለሚገኙ ወንድሞቻችን ጥሪ ላቀርብላቸው እፈልጋለሁ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛሬ አማራ መሪ አግኝቷል፤ አረጋ ከበደን የመሠለ ታማኝ ትጉህ መሪ አግኝቷል፣ አማራ ነኝ፣ ለአማራ እቆረቆራለሁ የሚል፣ የአማራ ጥቅም ሊነካ አይገባውም የሚል ሰክኖ በማሰብ ሕዝቡን እና ክልሉን መጥቀም የሚችል ሥራ መሥራት ይችላል ብለዋል።

በጫካ ለሚገኙ ወንድሞች መገዳደል፣ ይብቃን ጥፋት ይብቃን የኢትዮጵያን ሕዝቦች በእኩል የማያከብር ጉዞ ስለማይጠቅመን ኑ ወደ ክልላችሁ ተመለሱ፣ ክላችሁን አልሙ፣ ሰላማችሁን ጠብቁ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ያን ስታደርጉ እኛም በሙሉ ልብ ከጎናችሁ ሆነን አብረናችሁ እንሠራለን፣ በማይገባ ነገር መገዳደል ይበቃል ልላቸው እፈልጋለሁ ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፤ በብዙ ዓይነት ቁርሾ ቆይታለች፣ አሁን የሚያስፈልገን ነፃነት፣ ወንድማማችነት፣ እና መከባበር እንዲሁም እኩል ዜጋ ሆኖ ኢትዮጵያን በጥረት መገንባት ነውና ይህችን ታላቅ ሀገር ክብሯን ጠብቀን ለልጆቻችን ማሻገር እንድንችል ከጎናችን እንድትሆኑ ለአማራ ሕዝብ እና መንግሥት አደራ ማለት እፈልጋለሁ ብለዋል።

የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር መሪዎች ያማያልፍ ዐሻራ እንዲያኖሩ አደራ ብለዋል። ኢትዮጵያን የሚመጥን ድልድይ በውቧ ከተማ ማስቀመጥ ለቻሉ ባለሙያዎች እና መሪዎች ምስጋና አቅርበዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ ካልተጋነነ በመላው አፍሪካ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ድንቅ የጎርጎራ ፕሮጀክት ለሁለት ቀናት ማሳለፋቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የጎርጎራን ያክል ጠንካራ፣ ውብ እጅግ አስደማሚ ሥራ እስካሁን አላየንም ነው ያሉት።

የጎርጎራን ፕሮጀክት እንዲያዩ እና እንዲጠብቁ አደራ ብለዋል። ብዙ የምንጀምረው እና የምናጠናቅቀው ሥራ አለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን ሆኖ እንዲያግዝም ጥሪ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽዱ ኢትዮጵያ ጽዱ ከተማ ለመገንባት በአንድ ጀምበር 50 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ እየተሠራ ባለው ሥራ ሁሉም እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል ሲል የዘገበው አሚኮ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጦርነት ስብከቶች እና ፉከራዎች ጆሮ ይነፈጉ!

ሰላም ከፍ ያለ ሠብዓዊ እሴት ነው። ከዚህ የተነሳም በየዘመኑ ስለሰላም ብዙ ተብሏል ፤ ተዘምሯል ። በተለይም ዓለም በተለያዩ ምክንያቶች የከፉ ጦርነቶችን ለማስተናገድ መገደዷን ተከትሎ ጦርነቶች በሰው ልጅ ሁለንተናዊ ፍላጎቶች ላይ ከፈጠሩት አሉታዊ ተጽእኖ አኳያ ስለሰላም የሚደረጉ ዝማሬዎች ጎልተው መደመጥ ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

በአሁናዊው ዓለም የሰው ልጅ ከደረሰበት የአስተሳሰብ ልእልና አንጻር ፤ ለግጭት እና ለጦርነት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን በውይይት እና በድርድር በሰላማዊ መንገድ መፍታት የተለመደ እና የመሰልጠንም አንዱ መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ህሊና እንዳለው ፍጡርም ከራስ አልፎ ለሌሎች ማሰብን የሚያመላክት ሰው የመሆን ምልክት ነው።

በተለይም ግጭቶች እና ጦርነቶች ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የጥፋት አድማሳቸው ባየለበት በዚህ ዘመን ፤ ጦርነትን በማውገዝ ፤ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ፤ በእጅጉ የሚበረታታ ነው ። ለውጤታማነቱም የሚደረግ የትኛውም አይነት ድጋፍ ለሰው እና ለሠብዓዊነት ያለን ክብር አግዝፎ የሚያሳይም ነው ።

በተለይም እንደኛ ባሉ የታሪካቸው አብዛኛው ክፍል በግጭትና በጦርነት የተሞሉ ሀገራት ሕዝቦች ፤ ጦርነትን እና የጦርነት ድምጾችን አብዝተው ማውገዝ፤ ስለጦርነት ለሚደረጉ ስብከቶች እና ፉከራዎች ጆሮውን መንፈግ አለባቸው። ቀጣይ ሀገራዊ እጣ ፈንታቸውን ማስቀጠል የሚችሉት ይህን ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው።

እነዚህ ሀገራት በአንድም ይሁን በሌላ በቀደሙት ጊዜያት ከገቡባቸው ጦርነቶች ከደረሰባቸው ሁለንተናዊ ጥፋት /ጉዳት አኳያ ስለጦርነት አስከፊነት የማንንም ምስክርነት የሚሹ አይደሉም ፤ የጦርነት አስከፊ ገጽታ በሁለንተናዊ መልኩ በራሳቸው ደርሶ አይተውታል። ብዙ ወንድሞቻቸውን በሞት አጥተዋል፤ አካለ ጎዶሎ ሆነው አይተዋል ፤ ለዘመናት የደከሙበትን ሀብት እና ንብረት አጥተው ተረጅም ሆነዋል።

እንደ ሀገር ይሁን እንደ ግለሰብ በብዙ ተስፋ የጀመሩት የሕይወት ጉዞ ተሰናክሎ ለከፋ ረሀብ እና እርዛት፤ ለስደትና ለተስፋ መቁረጥ ተዳርገዋል። ዛሬዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ነገዎቻቸውም ጦርነት የፈጠረው ጽልመት ተጭኗቸው ፤ አስፈሪና አስጨናቂ ሆነውባቸዋል። ብዙ ተስፋ አልባ ቀናቶችን በግራ መጋባት እንዲያሳልፉ ተገድደዋል።

ይህ እውነታ ለኛ ኢትዮጵያውያን እንግዳ አይደለም። በየዘመኑ ካሳለፍናቸው የጦርነት እና የግጭት ታሪኮች አኳያ የለመድነው ፤ እንግዳ ያልሆነ እና ከማኅበረሰባዊ ታሪካችን ሰፊውን ትርክት የያዘ ነው። እንደ ሀገር ስለ ሰላም ብዙ እያዜምን ፤ ከትናንት ስህተቶቻችን ለመማር ባለመፍቀዳችን አልለቅ ያለን፣ ተጣብቆ ፤ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እያስከፈለን የኖረ እና ያለ ሀገራዊ ችግር ነው ።

ሠብዓዊ እሴቶች ለዘመናት በባህል እና በሃይማኖቶች በስፋት እየተሰበኩ ባለበት ፤ የማኅበረሰቡ የለት ተዕለት መስተጋብር ውስጥ የሰላም ጉዳይ ዋንኛ አጀንዳ በሆነበት ሁኔታ ፤ ዛሬም ለሕዝባችን የሰላም እጦት ጉዳይ ትልቁ አጀንዳ እንደሆነ ነው። ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘም እየተፈጠሩ ያሉ ፈተናዎች ሕይወቱን በብዙ ዋጋ እያስከፈሉት ነው።

በተለይም በፖለቲካው ዓለም በአጋጣሚ ይሁን በጥሪ የተደባለቁ ልሂቃን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን ዋነኛ የፖለቲካ ስትራቴጂ ከማድረግ ይልቅ ፤ የአቅመ ቢስነት መገለጫ አድርገው የማየታቸው ፤ በዚህም የመታመናቸው እውነታ ፤ አጠቃላይ የሆነው ሀገራዊ የፖለቲካ ባህል ሰላማዊ እንዳይሆን አድርጎታል ። ኃይልን እና ሴራን መሠረት ያደረገ እንዲሆን አስገድዶታል።

በዚህም ከሁሉም በላይ ሰላማዊ ሕዝባችን በዘመኑ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል ሆኗል። ሀገርም እንደሀገር ከፍ ካለ የሥልጣኔ ማማ ወርዳ የድህነት እና የኋላቀርነት ተምሳሌት የሆነችበት የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንድትዳክር አድርጓታል። በብዙ መስዋዕትነት ያገኘናቸውን ነጻነት ምሉእ በሚያደርግ የብልጽግና ጎዳና እንዳትገኝ ተግዳሮት ሆኖባት ኖሯል።

በ21ኛው ክፍለዘመን ለሰላም የተዘረጉ እጆችን መቀበል አቅቷቸው የዘመናችን ፖለቲከኞች በጫሩት ጦርነት፤ ሕዝባችን ትናንት ላይ የቱን ያህል ዋጋ እንደከፈለ ለማስታወስ የሚከብድ አይደለም። ጦርነቱ ከፈጠረው ሠብዓዊ እና ቁሳዊ ውድመት አኳያ እንደ ሀገር ያስከተለው የልብ ስብራት ትልቅ የታሪክ ስብራት ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ከዚህ የትናንት ስብራታችን መማር ያልቻሉ ፤ ዛሬም ሰላምና ሰላማዊነትን አቅመቢስነት አድርገው የሚወስዱ ግለሰቦች እና ቡድኖች ፤ በማን አለብኝነት ፤ ኃላፊነት በማይሰማው የጥፋት መንገድ ተመልሰው ለመገኘት በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለጦርነት የሚያደርጉት ዲስኩር፤ እንደ ትናንቱ ለማንም እንደማይጠቅም በአግባቡ ሊያጤኑት ይገባል።

ከጦርነት አውርድ ፉከራ እና ቀረርቶ በስተጀርባ ያለው ፤ ሥልጣን በአቋራጭ የመያዝ ሆነ ፍላጎትን በኃል የመጫን መሻት፤ የሕዝቦችን በሰላም የመኖር መብት ከመገዳደር ባለፈ ፤ በነገዎቻቸው ላይ ያላቸውን ብሩህ ተስፋ የሚያጨልም ነው። ምንም አይነት ትርክት እና ትርጓሜ ቢሰጠው ፤ የቱንም ያህል ሕዝባዊ ካባ ቢደረብበት፤ በየትኛውም መመዘኛ ሕዝባዊ መሠረት የለውም፤ ሊኖረውም አይችልም!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## "ጽዱ ኢትዮጵያ እና ጤናማ ማህበረሰብ"

ግርማ ሞገስ

የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ጽዳት ነው። ጽዱ ማህበረሰብ ጤናማ ትውልድን በማፍራት አምራች ዜጋን መፍጠር ይችላል ። ያደጉት ሀገራት ተሞክሮም የሚመላከተው ይህንኑ ነው።

የዓለም የጤና ድርጅት ሰነድ እንደሚያትተው ምንም እንኳ ባለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች (LMICs) ውስጥ የዜጎች የጤና ሁኔታ የተሻሻለ ቢሆንም ፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በርካታ አዳዲስ እውነታዎችም ተፈጥረዋል።

የተለወጡ የጤና አጠባበቅ ፍላጎቶች፣ እያደጉ ያሉ የማህበረሰብ ጥያቄዎች አብረው መጥተዋል። እነዚህ ደግሞ ከፍ ያሉ የጤና ግቦችን፤ የተሻሻሉ የጤና ሁኔታዎችን እና የላቁ የማህበራዊ እሴቶችን ለመፍጠር አስገድደዋል። እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት ደግሞ አሁን ባለው አካሄድ መቀጠል በቂ አይደለም።

የጤና ሥርዓቱን ጥራት ለማሻሻል ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን (UHC) መነሻ ሊሆን ይችላል። ሽፋኑንና የገንዘብ ድጋፍን ከማስፋፋት በተጨማሪ ጥራትን ማሻሻል ለሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን እውን መሆን ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት መንግሥታትም ለጤናና ተያያዥ ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በተለይም ለጤና ጉድለት እንደአንድ መንስኤ የሚጠቀሰውን የአካባቢ ጽዳት መጓደልን ለማስተካከል ከፍተኛ በጀት ከመመደብ ጀምሮ ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ ሰፋፊ ንቅንቃቄዎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በተለይም በአካባቢ ጤና መጓደል ዋነኛ ምክንያት ቀዳሚ ተጠቂ የሚሆኑት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከመሆናቸው አኳያ፤ እነሱን መሠረት ያደረገ የጤናና የአካባቢ ጽዳት እንቅስቃሴ ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት ፤ እያንዳንዱ የጤናና የአካባቢ ጽዳት እንቅስቃሴዎች ከመጀመራቸው በፊት ሁሉም ሰዉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ማረጋገጥ እና ዝቅተኛ ኑሮ ላላቸው ዜጎች ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ዝቅተኛውን ማህበረሰብ ያላሳተፈ የአካባቢ ጽዳት ንቅናቄ ውጤት አይኖረውም።

በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጭነት የተጀመረው የጽዱ ኢትዮጵያ ኑሮ ለጤና ትብብር ንቅናቄ ይህን ሃሳብ የሚደግፍ ነው። እንደሚታወቀው በሀገራችን የአካባቢ ንጽህና ጉዳይ ብዙም የዳበረ ባህል አይደለም። በዚህ ምክንያትን በሚከሰቱ ችግሮች /በሽታዎች ምክንያት ተጠቂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በእጅጉ በርካታ ናቸው ።

ከጤና ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎች እንደሚ ጠቁሙት፤ ከ30 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጸዳጃ ቤት አይጠቀምም። ይህ በሚሊዮኖች የሚቆጠረው የሀገሬው ነዋሪ ወገቡን የሚፈትሸው በየጥሻውና በየጥጋጥጉ ነው። ይህ እንደ ሀገር በማህበረሰብ ጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው። ከግለሰብና ማህበረሰብ አልፎም ጦሱም ለሀገር የሚተርፍ ነው።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ እነዚህን የማህበረሰብ ጤና ችግሮች ለመቅረፍ ያለመ ነው። ንቅናቄው እንደ ሀገር በርካታ ተቋማት ተቀብለው እያስቀጠሉት ይገኛሉ። ንቅናቄው በጠንካራ ዲሲፕሊን እና በሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ ከተመራ የማህበረሰብን ጤና ለማሻሻል ሁነኛ መፍትሄ ሊሆን የሚችል ነው።

የ "ጽዱ ኢትዮጵያ" ንቅናቄ አካል የሆነው የጽዱ ጤና ተቋማት ንቅናቄ ከጀመሩት የፌዴራል ተቋማት መካከል የጤና ሚኒስቴር አንዱ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበረውና "የጽዱ ኢትዮጵያ ጽዱ ጤና ተቋማት ለተሟላ ጤንነት" በሚል መሪ ሃሳብ የያዘውን የአካባቢ ጽዳትና ንፅህናን የማሻሻል እንቅስቃሴ በተለያዩ ሆስፒታሎችም ተጀምሯል። ይህም ንቅናቄ ሆስፒታሎችን ንፁህ በማድረግ ኅብረተሰቡን ጤናማ ለማድረግ የሚያስችልም ይሆናል።

### ጤናማ ለመሆን ንጽህናን ከራስ በመጀመር ወደ አካባቢ ከዛም ወደ ሀገር ማስፋት ይጠበቃል

ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል የጽዱ ጤና ተቋማት ንቅናቄ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ጤናማ ለመሆን ንጽህናን ከራስ በመጀመር ወደ አካባቢ ከዛም ወደ ሀገር ማስፋት ይጠበቃል። ይህንንም በያገባኛል ስሜት በጋራ መሥራት እንዲቻል የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በስፋት መሥራትን ይሻል።

እንደ ሀገር ለሁሉም ዜጎች ምቹ የሆኑ ከተሞችን መፍጠር የሚቻለው የነቃና የጤና ችግሮችን መለየት የሚችል ማህበረሰብ መፍጠር ሲቻል ነው። ለዚህ ደግሞ የማህበረሰቡን የጽዳት ባህል ክብርን የጠበቀ ለማድረግ የተወጠነው የጽዱ ኢትዮጲያ ንቅናቄ፤ መጸዳጃ ቤቶችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ መገንባትን ያለመ ነው።

ከተማን ውብ፣ ፅዱና ለነዋሪዎቿ ምቹ የማድረግ አካል ተደርጎ የተጀመረው የ "ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና" የሚል አዲስ ሃሳብ የአፍሪካውያን መዲና በሆነችው አዲስ አበባ በሰፊው እየተተገበረ ይገኛል። ይህ አዲስ ንቅናቄ ነዋሪዎቹን በሚያሳቅቅና አንገት በሚያስደፋ መልኩ በየመንገዱ፤ በየህንጻው ስር መፀዳዳትን በማስቆም የከተማ ውበት በሚጨምር ሁናቴ ፣ ጤናማ አካባቢንም ለመፍጠር የሚያስችል ነው።

ይህ ተነሳሽነት "ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና" በሚል መሪ ቃል በገንዘብ ወይንም በዓይነት የኅብረተሰብ ድጋፍ ማድረግ እንደሚቻል የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስታውቋል። በዚህም ንቅናቄ በርካታ ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል። በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የተጀመረው የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በመተግበር ሁሉም ዜጎች በየደረጃቸው አቅማቸው በፈቀደው ድጋፍ በማድረግ አካባቢን ለጤና ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ በዓለም ባንክ ድጋፍ በሀገሪቱ 22 ከተሞች ከማኅበረሰብ የንጽህና አጠባበቅ ጋር በተያያዘ በመከናወን ላይ የሚገኙ የውሃና የመጸዳጃ ቤት ፕሮጀክቶች በተለያዩ ከተሞች በመገንባት ላይ ናቸው። ፕሮጀክቶቹ የመጸዳጃ ቤት ሽፋኑን በፈረንጆቹ 2030 ዓ.ም ወደ መቶ ፐርሰንት ለማድረስ የሚያግዙ ናቸው። እነዚህ የተቀናጁ ጥረቶች ሙሉ ለሙሉ ሲተገበሩ እንደ ሀገር ንጹህና ጽዱ አካባቢን በመፍጠር ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ዜጋን መፍጠር የሚያስችል ይሆናል።

# ነፃ ሃሳብ

## ጽዱ ጎዳናዎችን ለማየት

**እስማኤል አረቦ**

ባዶ ሜዳ ላይ መጸዳዳት ዓለም አቀፍ ችግር ነው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በዓለማችን ላይ 467 ሚሊዮን ሕዝብ በሜዳ ላይ ይጸዳዳል። በኢትዮጵያ ደግሞ 30 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ መጸዳጃ ቤት የለውም። ይህም ማለት ደግሞ ባዶ ሜዳ ላይ ይጸዳዳል ማለት ነው።

ይህ ሀገራዊ ችግር ብሶ የሚገኘው መዲናችን፣ አዲስ አበባ ላይ የመሆኑ ጉዳይ ችግሩን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፤ የአፍሪካ መዲናና ከኒዮርክና ጄኔቫ ቀጥላ ሶስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ በየሜዳው መጸዳዳት እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ማህበራዊ ጉዳይ አይደለም።

ከተሞች ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መቀመጫነት ሊመረጡ የሚችሉት በቀዳሚነት ጽዱና ውብ ሲሆኑ ነው። ጽዱና ውብ ያልሆኑ ከተሞች ለማንኛውም አገልግሎት ተመራጭ አይሆኑም። ስለዚህም ከ50 ዓመታት በላይ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ሆና የቆየችው አዲስ አበባ በጽዳቷ ምክንያት መቀመጫነቷ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

በግልፅ እንደሚታወቀው፣ ባዶ ሜዳ ላይ መጸዳዳትና አካባቢን መበከል በርካታ የሆኑ ውስብስብ ችግሮችን ያስከትላል። ባዶ ሜዳ ላይ የሚጸዳዳ ማህበረሰብ ክብር የለውም። የሰው ልጅ እራሱን ከእይታ ከልሎ ከሚያከናውናቸው ተፈጥሯዊ ተግባራት መካከል አንዱና ዋነኛው መጸዳዳት ነው።

ከዚህ ውጪ ሲሆን ክብርን ያጎድፋል፤ ከሰው ልጅ ተርታ አስወጥቶ ከእንስሳት ተርታ ያሰልፋል። ያውም ደግሞ የድመትን ያህል እንኳን ክብር ያሳጣል። ከዚህም ባሻገር እንደ ኢትዮጵያዊነትም ክብርን ዝቅ የሚያደርግና የጀግንነት ተጋድሎ ላይ ጥላ የሚጠላ ነው።

ኢትዮጵያ የጀግኖች መፍለቂያ ናት። በየዘመናቱ የሀገሬን ሉአላዊነትና ዳር ድንበር አላስደፍርም ያሉ ጀግኖች ልጆቿ እምቢ ለሀገሬ በማለት አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍሰውና ህይወታቸውን መስዋዕት አድርገው የሀገራቸውን ሉአላዊነት አስጠብቀዋል፤ ለተተኪው ትውልድም አስረክበዋል።

ኢትዮጵያ ታሪካዊት ሀገር፤ ሕዝቧም የዚህ ታላቅ ጀብዱ ባለቤት ነው። ይህ ጀግና ሕዝብ ደግሞ ስሙ ሁልጊዜ ሲነሳ የሚሰማው ከመልካም ነገሮች ጋር ነው። ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር እንጂ ኢትዮጵያ ‹‹ሕዝቧ ሜዳ ላይ የሚጸዳዳባት ሀገር›› ተብላ መነሳት የለባትም፤ ክብሯንም የሚመጥን አይደለም።

ከዚሁ ሁሉ በሻገርም ኢትዮጵያዊነት ኩሩነት ነው። ኢትዮጵያ ለጊዜው ድሃ ብትሆንም ክብሯን አሳልፋ የምትሰጥ ሀገር ግን አይደለችም። የኢትዮጵያዊነት መገለጫም ጀግነነትና ክብር ነው። አንድ ኢትዮጵያዊ ድሃ ቢሆንም በክብሩ ግን ድርድር አያውቅም። ለአንድ ኢትዮጵያዊ ቆሻሻ መባል ሞት ነው።

ይህ ደግሞ ከባህል፣ ከእምነትና እሴት ጋር የተያያዘ ነው። ኢትዮጵያዊያን ነውራቸውን መደበቅ፤ አፀያፊ ተግባራትን ማውገዝና አርአያነት ያለውን ተግባር መፈጸም መለያቸው ነው። በየሜዳው መጸዳዳት ከዚህ ኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር የሚጣረስና እንደ አረም የወረረ አፀያፊ ተግባር ነው።

የጽዳት ጉዳይ ከዓለማዊ አልፎ ሰማያዊ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ከ98 በመቶ በላይ የሆነው ሕዝብ አማኝ ነው። ይህ አማኝ ሕዝብ የሚከተላቸው ሃይማኖቶች ለንጽህና ከፍተኛ ክብርን የሚሰጡ ናቸው። በክርስትናም ሆነ በእስልምና እምነቶች ንጽህና ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል።

በየሜዳው የሚጸዳዳ ማህበረሰብ ክብር ከማጣቱም ባሻገር ኋላ ቀር ተደርጎ ይቆጠራል። ጽዳት የስልጣኔ አንዱ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ክብር ሳይጠብቁ በየሜዳው መጸዳዳት ከስልጣኔ መራቅን እና ኋላ ቀር መሆኑን ያሳያል። ዓለም በስልጣኔ መጥቆ፤ ከመሬት አልፎ ጠረፍ ላይ ምርምር በሚያደርግበት በዚህ ዘመን የሰው ልጅ ሜዳ ላይ ሲጸዳዳ መገኘቱ

> ይህ ጀግና ሕዝብ ደግሞ ስሙ ሁልጊዜ ሲነሳ የሚሰማው ከመልካም ነገሮች ጋር ነው። ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር እንጂ ኢትዮጵያ ‹‹ሕዝቧ ሜዳ ላይ የሚጸዳዳባት ሀገር›› ተብላ መነሳት የለባትም፤ ክብሯንም የሚመጥን አይደለም

እንደጋርዮሽ ዘመን ሰው የሚያስቆጥረው ነው።

ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ስልጣኔን የምናውቅና በርካታ ቁም ነገሮችን ለዓለም ሕዝብ ያስተዋወቅን ከመሆኑ አንጻር፣ 30 ሚሊዮን ሕዝብ ሜዳ ላይ ወጥቶ መጸዳዳቱ ከስልጣኔ እየሸሸን መምጣታችንን የሚያሳይ ነው። ጽዳት ከክብርም በላይ የስነልቦናም ጦስ ይዞ ይመጣል።

ጽዱ ያልሆነ ማህበረሰብ የስነልቦና የበላይነት አይኖረውም። ደረቱን ነፋ አድርጎ መናገርና ከሰው ፊትም መቆም አይችልም። በየቦታው ተጸዳድቶ፤ ቆሻሻ ለቦሶና ቆሻሻ ተመግቦ መኩራራት አይቻልም። ቆሻሻ በሆኑ ቁጥር ሁልጊዜ የበታችነት ስሜት አለ። ሰፊው ሕዝብ ሜዳ ላይ የሚጸዳዳባት ሀገር እንደ ሀገርም ለዛች ሀገር ውርደትን ያስከትላል።

በየትኛውም መድረክ ላይ ተገኝቶ የሀገርን ገጽታ ለመገንባት ይቸገራል። በስነልቦና የተሸነፈ ሀገር ደግሞ በሁሉም ዘርፍ ተሸናፊ መሆኑ አይቀርም። የጽዳትና የንጽህና መጓደል የሀገርን ገጽታ የሚያበላሽና ቱሪዝምንም በእጅጉ የሚጎዳ ነው። የቆሸሸን ሀገር ለመጎብኘት የሚመኝ ማንም ቱሪስት የለም። ቱሪስቶች ለመጎብኘት የመጀመሪያ ምርጫ የሚያደርጉት ውብና ንጹህ አካባቢን ነው።

ኢትዮጵያ ለቱሪዝም የሚሆኑ በርካታ ጸጋዎች ያሏት ሀገር ነች። ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት ነች። የተፈጥሮ ሀብቶቿ ከኤርታኢሌ እስከ ዳሎል፤ ከራስ ዳሽን እስከ ታችኛው ኦሞ ሸለቆ ድረስ የተዘረጉ ናቸው። ከእነዚህም መካከል አስደናቂ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም የሰው ዘር መገኛ ስፍራዎች ተካተውባታል።

ሃይማኖታዊ በዓላትም የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሆነው እና በዩኒስኮ ደረጃ ተመዝግበው ዛሬ የዓለም ቅርስ እስከ መሆን ደርሰዋል። በአፍሪካም ቅርሶችን በማስመዝገብ ቀዳሚ ሀገር ነች። እነዚህ ቅርሶች ለጎብኚዎች መስህብ ሊሆኑ የሚችሉት የሀገሪቱ ጽዳት ሲጠበቅ ነው። ኢትዮጵያ ጽዱና ውብ እስካልሆነች ድረስ እነዚህ አማላይ የቱሪዝም መስህቦች የጋን ውስጥ መብራት ከመሆን የዘለለ ፋይዳ የላቸውም።

በተለይም በአሁኑ ወቅት መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ቱሪዝምን እንደዋነኛ የገቢ ምንጭ በወሰደበት ወቅት በጽዳት መጓደል ምክንያት የሚጠበቀው ገቢ ሲታጣ እንደ ሀገር ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢ ይሆናል።

በንጽህና መጓደል ተላላፊ በሽታዎች ሲከሰቱ ቱሪስቶች ሁልጊዜ ጉዟቸውን ይሰርዛሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ ሀገር በርካታ ዶላሮችን ታጣለች። በዚህ ምክንያት የገንዘብ እጥረት ይከሰትና ሊሰሩ የታሰቡ መሰረተ ልማቶች ይታጠፋሉ። የትምህርትና የጤና ተቋማት በበጀት እጥረት የተነሳ ስራቸው ይስተጓጎላል፤ የመንገድ መሰረተ ልማት ይቋረጣል። የታሰበው እድገትና ብልጽግና ህልም ሆኖ ይቀራል። ከዚሁም ጋር ተያይዞ ኢንቨስትመንት ይዳከማል።

የውጭ ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን ማፍሰስ የሚፈልጉት ጽዱና ጤናማ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ ነው። ኢንቨስተር (ባለ ሀብት) ጤናው የተጠበቀና አምራች የሰው ኃይል ይፈልጋል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ አካባቢውን በአግባቡ የሚያጸዳ እና ለጤናው ትኩረት የሚሰጥ ዜጋ ሲበራከት ነው።

የአካባቢ ጽዳት መጓደል ከሁሉ በፊት የሚጎዳው ጤናን ነው። በኢትዮጵያ 48 በመቶ የሚሆኑት በሽታዎች የሚከሰቱት ከአካባቢ ጤና መጓደል ጋር በተያያዘ ነው። ከጤና ጥበቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በየሜዳው የሚደረገው መጸዳዳት ከፍተኛ የጤና ቀውስ እያስከተለ ይገኛል። በርካቶችንም ለህልፈተ ሕይወት እየዳረገ ነው።

ተላላፊ በሽታ ከሰው ወደ እንስሳት ወደ ሌላ ሰው ወይም እንስሳት ይተላለፋል። ሁሉም ተላላፊ በሽታዎች በዓይን የማይታዩ እንደ ባክቴሪያና ቫይረስ ያሉ ተዋህሲያን እና ጥገኛ የአንጀት ትላትሎች አማካይነት የሚከሰቱ ናቸው። አብዛኛዎቹ ለጤና ጐጂ የሆኑ ተዛማች ተህዋሲያን በበሽታ በተጠቁ ወይንም ተሸካሚ በሆኑ ሰዎች አይነ-ምድር ውስጥ ይገኛሉ። ከአይነ-ምድር ጋር የሚወጡት እነዚህ ጀርሞች በተለያዩ መንገዶች ወደ ሌላ ሰው በመዛመት በሽታን ያስከትላሉ።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከዩኒሴፍና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተባባሪ አካላት ጋር ያጠናው ጥናት እንደሚያሳየው ደረጃቸውን ያልጠበቁ የመፀዳጃ ቤቶች፣ የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና አጠባበቅ እና ያልተሟላ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴ ዋና ዋና የጤና ችግሮች መንስኤ ናቸው።

ምንም እንኳን የመፀዳጃ ቤቶች ሽፋን የጨመረ ቢሆንም የጥራትና የአጠቃቀም ችግሮች መስተዋላቸው አሌ የሚባል አይደለም። በገጠር 19% የሚሆን ሕዝብ ብቻ የተሻለ መፀዳጃ ቤት የሚጠቀም ሲሆን፣ 6% የጋራ፤ እንዲሁም 22% ደግሞ መስፈርቱን ያላሟሉ መፀዳጃ ቤቶችን ይጠቀማል። ወደ 53% የሚሆኑ ዜጎች በሜዳ ላይ ይፀዳዳሉ። በተለይም፣ በጣም ተዛማች የሆኑ ተላላፊ በሽታዎች ማለትም ተቅማጥና ኮሌራ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ በኢትዮጵያ ለሞት የሚዳርጉበት ምስጢርም ይኸው ነው። የተቅማጥ በሽታዎች በየዓመቱ የ2.2 ሚሊዮን ሰው ህይወትን የሚቀጥፉ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል 85% ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው።

በአጠቃላይ ሜዳ ላይ መጸዳዳት አደጋው ዘርፈ ብዙ ነው። ይህንኑ በመረዳት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት ‹‹ጽዱ ጎዳና፤ ኑሮ በጤና›› ንቅናቄ ይፋ ሆኗል። ይህ ንቅናቄ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን የሚያሳትፍና መጸዳጃ ቤቶችንም የማስፋፋት አላማ ያለው መሆኑ ተገልጿል። ይህ ንቅናቄ አብዛኛው ማህበረሰብ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክትና እንደ ሀገርም በየቦታው መጸዳዳት እያስከተለ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግር መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ነው።

ይህ ንቅናቄ እንደ ሀገር የተጀመረውን የ“ጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ዳር ለማድረስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የብዙዎች እምነት ነው። የመፀዳጃ ቤት ችግሩን ለመፍታት እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው። ዜጎችን አስተባብሮ ደረጃቸውን የጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች እንዲገነቡም ዕድል የሚሰጥ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም ሜዳ ላይ መጸዳዳት ጸያፍ፤ የሀገርና የሕዝብ ክብርን ዝቅ የሚያደርግ መሆኑን የሚያመላክቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችንም የሚያካትት ነው።

ባለሙያዎች አብዛኛው በሜዳ የመጸዳዳት ልምድ ያለው ማህበረሰብ ሲያጋጥም ጠንከር ያለ የትግበራ ስልት ሊኖር እንደሚገባ ይመክራሉ። በኢትዮጵያ በመተግበር ላይ ያለው አንዱ የትግበራ አካሄድ ማህበረሰብ መር ጠቅላላ ሳኒቴሽን (CLTSH) ነው። ይህ የትግበራ አካሄድ ስሜትን የሚቀሰቅሱ ሀፍረተ ቃላትን በመጠቀም በሜዳ የመጸዳዳትን ልምድ ጨርሶ የማጥፋት እና የባህሪይ ለውጥ ማምጣጥ የሚያስችል ነው።

አካሄዱ መጸዳጃ ቤት ከመገንባት ጎን ለጎን የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ የሚያስችል፤ እራሱን፣ ማህበረሰቡን በማሳተፍ እና ሂደቱን እንዲመራ በማድረግ በሜዳ ከመጸዳዳት ሙሉ በሙሉ የፀዳ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያግዝ ነው። በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው ማህበረሰቡ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲጠቀም፣ ወሳኝ በሆኑ ጊዜ እጅን በሳሙና ወይም በአመድ መታጠብ፤ አስተማማኝ የቤት ውስጥ ውሃ አያያዝና አጠቃቀም ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል (በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኙ ማህበረሰብ፣ የእድሜ ክልል፣ ፆታ ወዘተ) የሚጨምር ነው።

ስልቱ ማህበረሰቡ ባህልና ወጉን መለስ ብሎ እንዲመለከት፤ ሰብአዊ ክብሩን በውል እንዲገነዘብና ውስጡን እንዲጠይቅ የሚያደርግ ነው። ያለ ምንም መደባበቅ ሀፍረተ ቃላትን በመጠቀም ‹‹ባዶ ሜዳ ላይ መጸዳዳት ነውር›› መሆኑን ደጋግሞ በመንገር በሜዳ ላይ መጸዳዳትን መቶ በመቶ ማስቀረት ይገባል። አሁን እንደ ሀገር ችግሩን ለመፍታት የተጀመሩ ንቅናቄዎች ጎን ለጎንም ማህበረሰቡ ወግና ባህሉን፤ እንዲሁም፣ ክብሩን እንዲጠብቅ የሚያስችሉ የግንዛቤ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# በተስፋና በስጋት የታጠረው የዱኤሻገላ አርሶአደሮች የሙዝ ልማት

**ማህሌት አብዱል**

አቶ ሹክራላ ሃጂሉል ባሮ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሃድያ ዞን ሻሸጎ ወረዳ የዱኤሻገላ ቀበሌ አርሶ አደር ናቸው። እሳቸውም ሆኑ መላው የዱኤሻገላ አርሶ አደሮች በቆሎና መሰል አዝዕርቶችን በአመት አንዴ ብቻ ያመርቱ ነበር። ይህ ደግሞ እንኳን ገበያ አውጥተው ሊሸጡት ይቅርና ለቤተሰባቸውም በቂ አልነበረም።

በዚህ ምክንያት ሁልጊዜም ቢሆን የመንግሥት እጅ ጠባቂ ነበርን ሲሉ አቶ ሹክራላ ይገልጻሉ። ከአራት ዓመታት ወዲህ በክልሉ በተፈጠረው መነቃቃት ሌሎች ሰብሎችንና ፍራፍሬዎችን እንዲያመርቱና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሰፊና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መከናወናቸውን ያመለክታሉ።

በተለይም ደግሞ የአካባቢያቸው የአየር ንብረት ለፍራፍሬ ምርት ምቹ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እሳቸውና ሌሎች የተመረጡ አርሶአደሮች አርባ ምንጭ ሄደው ተሞክሮ መቅሰማቸውን ይጠቁማሉ። የሙዝ ችግኝ አምጠተው በማሳቸው ላይ ተከሉ፤ ብዙ ጊዜ ሳይወስድም ፍሬውን ማየት መቻላቸው ይበልጥ ትኩረታቸውን በሙዝ ችግኝ ላይ እንዲያደርጉ እንዳነሳሳቸው ይገልፃሉ። እናም ማሳቸውን በማስፋፋት ከቤት ፍጆታ አልፎ ለገበያ በማቅረብ የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ እንዳስቻላቸው ያብራራሉ።

‹‹መጀመሪያ ላይ ሙዝ አምጥቼ ስተክል ብዙ የአካባቢያችን አርሶአደሮች ተቃውመውኝ ነበር፤ ጥቂት የማይባሉትም ለትከስር ትችላለህ ብለው አስፈራርተውኛል፤ ሆኖም ዘጠኝ ወር ባልሞላ ጊዜ ምርት ማየት ስጀምርና በሙዙ ተጠቃሚ መሆን ስንችል አመለካከታቸው ተቀየረ፤ የእኔን ተሞክሮ አይተው ብዙዎቹ ችግኝ እንድሰጣቸው ጠይቀውኝ ተክለዋል›› ይላሉ። በዋናነት ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት የብላቴን ወንዝ በመጠቀም በመስኖ ማልማት በመቻላቸው ውጤታማ እንደነበሩ ያስታውሳሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአካባቢው ዋነኛና ብቸኛ የመስኖ አውታር የሆነው የብላቴ ወንዝ ግድቡ በመሰበሩና አቅጣጫውን ከመሳቱ ጋር ተያይዞ በመስኖ የሚመጣላቸው ውሃ መመናመኑን ጠቅሰው፣ በዚህ ምክንያት በተለይ አዳዲስ የተከሏቸው የሙዝ ችግኞች የደረቁባቸው መሆኑን ያስረዳሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ቶሎ እልባት ካልተሰጠው የማሳቸውን ሙዝና ሌሎች ፍራፍሬዎች በሙሉ እንዳይጠፉባቸው ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ነው ያብራሩት።

ሌላው አርሶአደር ይቴቦ ሽጉጤ በበኩላቸው ፤በክልሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተጀመረበት ወቅት የቀበሌው ሊቀመንበር ሆነው ሰርተዋል፤ ሙዝ የማልማት ሃሳብ በግብርና ቢሮው ሲቀርብ አርሶአደሩ ፈፅሞ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልነበረ አርሶ አደር ይቴቦ ያስታውሳሉ። የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ከተሰራ በኋላ እሳቸው ለሌሎች አብነት ለመሆን በማሰብ ቀድመው በራሳቸው ማሳ ላይ ሙዝ መትከላቸውን ይጠቁማሉ።

ሙዙ እስከሚያፈራ ድረስም ጎን ለጎን ቶሎ የሚደርሱ እንደጎመን ያሉ ሰብሎችን በመትከል ተጠቅመዋል። ‹‹ሙዙ ከሰባት ወር በኋላ ምርት መስጠት የጀመረ ሲሆን፤ የመጀመሪያውን የምስራች ያየነው በእኔ ማሳ ነበር›› ሲሉ ይናገራሉ። ይህንን ያዩ አርሶአደሮች መነሳሳት ተፈጥሮባቸው ችግኝ ከእሳቸው ወስደው መትከላቸውን ገልጸዋል።

አርሶአደር ይቴቦ እንደሚሉት፤ መጀመሪያ ላይ ሰባ የሙዝ ችግኝ ብቻ የተከሉ ሲሆን፤ ውጤቱን ካዩ በኋላ ግን የሙዝ ልማቱን በማሳቸው ላይ አስፋፍተዋል። በተጓዳኝም ሌሎች የጓሮ አትክልቶችን የሚያለሙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ምርቱ የቤተሰባቸውን የምግብ ፍጆታ ሙሉ ለሙሉ ማሟላት አስችሏቸዋል። አንዱን የሙዝ ግንድ ከ400 እስከ 500 ብር በመሸጥ ከሳምንት ሳምንት የማይቋረጥ የገቢ ምንጭ ሆናላቸዋል።

ከሙዙ ባሻገር አቦካዶና ቡና ጭምር አምርተው በመሸጥ የገቢ አቅማቸውን የሚሳድጉበት እድል ተፈጥሮላቸዋል።ከዚህ ባሻገርም ከእሳቸውና ከሌሎች አርሶ አደሮች ማሳ ዘጠኝ ሺ የሙዝ ችግኝ በማሰባሰብ ለወረዳው የምግብ ዋስትና በመሸጥ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉበትን ሁኔታ ጠቅሰዋል።


ፎቶ- ዳኜ አበራ

‹‹ዘንድሮ በመስኖ ግድቡ ላይ በጎርፍ በደረሰ ጉዳት መቀልበሻው በመሰበሩ የውሃ እጥረት አጋጥሞናል፤ በዚህ ምክንያትም ምርት ቀንሶብናል፤ ችግኝም እጥተን መሸጥ አልቻልንም›› የሚሉት አርሶአደር ይቴቦ፤ ከዚህ ቀደም በስንዴ ይሸፈኑ የነበሩ ማሳዎች አሁን ላይ በተከሰተው ችግር ፆም ያደሩበት ሁኔታ መፈጠሩንም ጠቁመዋል። ይህም በአርሶአደሩ ህይወት ላይ ስጋት የጋረጠበት መሆኑንና ቶሎ መፍትሔ ካልተሰጠው ችግሩ ከዚህም በላይ ሊብስ ይችላል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ቀድሞም ቢሆን ሲያንገራግር የነበረው የአካባቢው አርሶአደር ሰፊ የአመለካከት ክፍተት ያለበት መሆኑን ጠቅሰው፣ የክልሉ አመራር ግድቡን ከመጠገን ባለፈ አርሶአደሩ ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መስራት እንደሚገባው አርሶአደር ይተቦ ያስገነዝባሉ። ‹‹በተለይም በክላስተር ተደራጅቶ ማልማት ያለውን ጠቀሜታ አርሶአደሩ በአግባቡ ባለመገንዘቡ ምክንያትና ሁሉም በተናጠል የሚለፋ በመሆኑ ብዙ ሃብትና ጉልበት እየባከነ ነው፤ ተደራጅተን ብንሰራ ግን በዋናነት በገበያ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን፤ ይህንን በሚመለከት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መሰራት ይገባል›› ሲሉም ያክላሉ።

የሻሸጎ ወረዳ ግብርና ፅህፈት ቤት እርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ ሜጊሶ በበኩላቸው፤ በዱኤሻገላ ቀበሌ ከብላቴ ወንዝ በሚገኘው ውሃ 4 ነጥብ 5 ሄክታር መሬት ላይ ሙዝ እንዲሁም 371 ሄክታር መሬት ላይ ደግሞ የበጋ መስኖ ስንዴ ይለማ እንደነበር ይጠቅሳሉ። እንዲሁም በርበሬ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲምና ሚጥሚጣ በስፋት ይለማ እንደነበርም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የክልሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኢኒሼቲቭ በሆነው 30-40-30 መርሀ-ግብር ሲጀመር በወረዳው 60 ሺ የሙዝ ችግኞች ተተክለዋል። አስር ቀበሌዎችን የያዘ አራት የፍራፍሬ መንደርም ተመስርቷል። በተለይ ዱኤሻገላ ቀበሌ የሙዝ ምርት በከፍተኛ መጠን በመስፋፋቱ ችግኙን ወደ ሌሎች ቀበሌዎች የማዳረስ ስራ ተሰርቷል።

አርሶአደሩ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ማምረት መጀመሩ የቤተሰቡን የምግብ ስርዓት የተመጣጠነ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ሚና ማበርከቱን ከዚያ ባሻገር የገበያ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆን ከቀበሌው አስተዳደር ጀምሮ ቅንጅታዊ ስራ መሰራቱን በዚህም ምክንያት ነጋዴዎች ማሳ ድረስ በመምጣት ምርቱን የሚገዙበት ሁኔታ መኖሩን ያስረዳሉ።

ከዱኤሾ ቀበሌ ውጪ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ግን ሰፊ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት በመኖሩ ልማቱ እንደቀጠለ መሆኑን ጠቅሰው፤ ‹‹በዚህም ቀበሌ ቢሆን ግድቡ ከተበላሸ በኋላ እንደ ሌሎቹ አይስፋፉ እንጂ በጉድጓድ ውሃ የማልማት ስራ የጀመሩ አርሶአደሮች አሉ›› ይላሉ።

እሳቸውም እንዳሉት፤ ግድቡ ብልሽት ከደረሰበት ወዲህ የቀበሌው ምርት ቀንሷል። ወንዙ ላይ ያለው ግድብ የተበላሸውም በ2015 ክረምት ላይ ሲሆን፣ ብልሽቱም ከክልል በመጡ ባለሙያዎች ጥናት ተደርጎበታል፤ ጠግኖ መልሶ ወደ ልማት ለማስገባት ወደ 40 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር የሚያስፈልግ ሲሆን፣ የተጠየቀውን ፋይናንስ በወረዳም ሆነ በዞን ደረጃ የሚቻል አይደለም። ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል የቀረበ ሲሆን፣ የክልሉ መንግሥትም በቅርቡ ጨረታ አውጥቶ ግድቡን ለመጠገን እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ብለዋል።

አቶ ታደሰ ሞኮሮ የሻሸጎ ወረዳ ምክትል አስተዳደሪና ግብርና ፅህፈት ቤት ኃላፊ ናቸው። እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ወረዳው የአየር ንብረቱም ሆነ ስነ ምህዳሩ ለግብርና ስራዎች ምቹ ከሚባሉት የዞኑ አካባቢዎች አንዱ ነው። ይሁንና አርሶአደሩ በዝናብ ጥገኝነት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚከተል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአካባቢው ማህበረሰብ ኑሮ ከእጅ ወደአፍ የሚባል አይነት ነበር። የብላቴ ወንዝ የመስኖ ግድብ ከተሰራ ከአስር ዓመት በፊት ቢሆንም አርሶአደሩ ተጠቃሚ አልነበረም።

ይሁንና እንደሃገርም ሆነ እንደክልል የተለያዩ የልማት መርሃግብሮች ይፋ ከተደረጉ ወዲህ ግን የወረዳውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ርብርብ ሲደረግ መቆየቱን ያስታውሳሉ። በተለይ ደግሞ የብላቴን ወንዝ በመጠቀም አርሶአደሩ የመስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት መደረጉን ያመለክታሉ።

የወረዳውን አርሶአደሮች ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ተግባራዊ ከሆኑት መርሃ ግብሮች መካከል የሌማት ቱሩፋት ዋነኛው ሲሆን፣ በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በዶሮ እርባታና ንብ ማነብ ስራዎች የማስፋፋት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

‹‹ከዚህ ባሻገርም የክልሉ 30-40-30 የአትክልት ፍራፍሬ ኢንሼቲቭ ስራ በይፋ የተጀመረው እዚሁ ሻሸጎ ወረደ ላይ ነው›› የሚሉት አቶ ታደሰ፤ መጀመሪያ ላይ አርሶአደሩ ቶሎ ለመቀበል ባለመቻሉ እንቅፋት ሆኖ እንደነበር ያስታውሳሉ። በተለይም በአካባቢው ሙዝ የማይታወቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሙዙ ባይበቅል ልንከስር እንችላለን የሚል ስጋት አርሶአደሩን ወደ ልማቱ እንዳይገባ ሰቅሶ ይዞት እንደነበረ አይሸሽጉም።

‹‹አርሶአደሩ መጀመሪያ ላይ ሙዝ ላለማምረት ከጠበቅነው በላይ ሲያንገራግርና ሁሉንም ነገር በጥርጣሬ ሲመለከት ስለነበር፤ እኛው ራሳችን እየገባን እየሰራን እና የባለሙያ ክትትል ቀን በቀን ታክሎበት በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ማየት ችለናል››ይላሉ።

ሙዙ ከተተከለ በኋላ ግን የአርሶአደሩ አሉታዊ አመለካከት በሂደት እየተለወጠ መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ‹‹መጀመሪያ ላይ በራሳቸው ማሳ ላይ የተከልነውን ሙዝ ውሃ ለማጠጣት እንኳን ፍቃደኛ አልነበሩም፤ እኛው ራሳችን እየመጣን ነበር የምናጠጣው›› የሚሉት አቶ ታደሰ፤ ውጤቱን ካዩ በኋላ ማገዝና እንዲያውም የማስፋፋት ፍላጎት እያደረባቸው መምጣቱን ያስረዳሉ። በክላስተር ተደራጅተው ሙዝና ስንዴን በስፋት ማምረት መጀመራቸውን ይገልጻሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በወረዳው በመደበኛም ሆነ በበጋ መስኖ ልማት 4 ሺ 50 ሄክታር የማልማት አቅም ያለ ሲሆን፤ ከዚያ ውስጥ 3ሺ897 ሄክታሩን ማልማት ተችሏል። በተጨማሪም በወረዳው በሙዝ ብቻ አራት ክላስተር አለ፤ ዱኤሻገላ አንዱ ክላስተር ሲሆን፤ በዚህም አርሶአደሩ የምግብ ዋስትናውን ከማረጋገጥ ባለፈ የገቢ ምንጩን ማሳደግ ችሏል። ከዚህ ባሻገር በሌማት ትሩፋቱም ሆነ በ30-40-30 የልማት መርሃግብር ለአካባቢው ስራአጥ ወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሯል። 50 የሚሆኑ ወጣቶች በግብርና ልማት ለመሰማራት ተደራጅተው እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ዘንድሮ በመስኖ አውታሩ ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ምርት መቀነሱን እሳቸውም አረጋግጠዋል። በዚህም ምክንያት 210 ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ ለማልማት ታቅዶ ማልማት የተቻለው 76 ነጥብ 5 ሄክታር መሬት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ይህንን ያህል ማልማት የተቻለውም አርሶአደሩ ባደረገው ርብርብ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የክልሉ መንግሥት በአፋጣኝ ወደ ሥራ ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀው፤ በቅርቡ በክልል ደረጃ በተደረገ ውይይት ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች መኖራቸውን ይናገራሉ። ‹‹ የመስኖ መሰረተ ልማቱን ዳግሞ ወደ ልማት ማስገባት ከተቻለ የተጀመረውን የልማት መርሀ ግብር አጠናክሮ የማስቀጠል ሥራ ይሰራል›› በማለት ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ተስፋ የተጣለበት ልዩ የመምህራን ስልጠና

**ግርማ መንግሥቴ**

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያረጋግጡት የአንድ ስልጠና፣ በተለይም የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና አቢይ አላማው ግልፅ ነው። እሱም መምህራን ወደ ሥራው ዓለም በሚገቡበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ፤ እንዲሁም፣ አቅማቸው ጎልብቶ የመማር ማስተማሩን ሂደት በአግባቡ እንዲወጡ ማድረግ፣ መምህራኑ ከስልጠናው በተጨማሪ አጋዥ መጽሐፎችን በማንበብና የተሻሉ ልምዶችን በመውሰድ የማስተማር ክህሎታቸውን አዳብረው የተማሪዎችንና የራሳቸውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በሙሉ አቅም እንዲሠሩ ማስቻል ነው። በተጨማሪም መምህራን ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በሚያስተምሩት ትምህርት ዙሪያ በቂ ዝግጅት አድርገውና ከተማሪዎቻቸው ቀድመው በመገኘት አርዓያ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው።

የስነ-ትምህርት ሣይንስ ምሁራን እንደሚነግሩን የመምህራን በቂ ዕውቀት ያለመኖር፣ ተዘጋጅቶ አለመግባት፣ ሰዓት አለማክበር፣ አለባበስ፣ የፀጉር አቆራረጥ፣ ንፅህና፤ እንዲሁም፣ ተማሪዎችን በአንድ ዓይን አለማየት ለተማሪዎች አለመረጋጋትና ለክፍል ውስጥ ፀጥታ መደፍረስ ቁልፍ ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም መምህራኑ ጊዜያቸውን በአግባቡ ሳይጠቀሙና የሚፈልጉትን ነገር ሳያደርጉ ከክፍል እንዲወጡ የሚገደዱበት ጊዜ አለ። እነዚህን ሁሉ ችግሮች ለመፍታት ስልጠና የግድ አስፈላጊ ይሆናል።

መምህራን በአግባቡ አቅደውና በቂ ዝግጅት አድርገው ወደ ክፍል ከገቡ በራስ በመተማመን ማስተማርና ተማሪውም የሚፈልገውን ዕውቀት እንዲጨብጥ ማድረግ እንደሚችሉ፤ መምህር በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ሁሌም የመልካም ነገር መሪ መሆን እንዳለበትና በማኅበረሰቡም ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚገባ፣ ለተሳለጠ የትምህርት አሰጣጥ መምህር ለተማሪው ተቆርቋሪ መሆን እንዳለበትና መቆርቆሩ ወደ አላስፈላጊ ነገር ሊመራው እንደማይገባም የስነ-ትምህርት ባለሙያዎች አፅንኦት ሰጥተው ይናገራሉ። ስልጠና እነዚህን ሁሉ ችግሮች እንደሚያቃልል እና የመማር-ማስተማሩን ስራ ወደ ተሻለ ደረጃ እንደሚወስደው ያስረዳሉ።

ለምሳሌ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በመጠቀም በክፍል ውስጥ ማስተማር፣ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት፣ ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት፣ ከተሰጠ በኋላ፤ እንዲሁም፣ የክፍል አያያዝን መሠረት ያደረገ ስልጠና እንደሚያስፈልግ፤ ይህም በቀላል እንግሊዝኛ ሰዋሰውን አስተካክሎ መጠቀም፣ ምሳሌዎችንና አያያዦችን በአግባቡ በመጠቀም ተማሪዎችን ማስተማር እንዲችሉ እንደሚያደርግ፤ የማስተማር ስነ-ዘዴ፣ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ የምዘና መስፈርቶች እንዲሁም ከስነ ምግባር አኳያ ያለው አጠቃላይ ሁኔታ በስልጠናዎች መዳሰስ ያለባቸው ስለ መሆናቸው በመምህራን ስልጠናዎች ወቅትና ሂደት ሊታሰብባቸው የሚገቡ መሆናቸውም በባለሙያዎቹ ይጠቀሳሉ።

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን እና የትምህርት ልማት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገደች ምሬሳ በዘንድሮው የ50 ሺህ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና ሂሳብ፣ እንግሊዝኛ እና ሳይንስ ልዩ ትኩረትን እንደሚያገኙና ከሌሎቹ በተለየም በእነዚህ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ገልጸዋል።

ከአንድ ስልጠና አንድ መምህር ወደ ክፍል ከመግባቱ በፊት የማስተማሪያ እቅድ ማቀድ፣ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣ ለትምህርት ይዞቱ ማውጣት ያለበት ፈተና፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ከተማሪዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት፣ የሰዓት አጠቃቀምና አለባበስን ጨምሮ ትልቅ ግንዛቤ ይዞ ሊወጣ የሚገባ ስለመሆኑም ስለ ስልጠናዎች አስፈላጊነት በተነሳ ቁጥር ሳይጠቀሱ የማይታለፉት ናቸው።

ወደ ትምህርት ተቋማትም ስንመጣ የምናገኘው የስልጠና አስፈላጊነትን ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ተልዕኮው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ጥራት፣ ተገቢነትና በኢንዱስትሪው መሪነት የባለሙያዎች የሙያ ብቃት በምዘና በማረጋገጥ ደረጃውን የጠበቀ ብቁና ተወዳዳሪ



ወይዘሮ አሰገደች ምሬሳ፣

ትምህርትና ሥልጠና ተቋም እና ባለሙያ መፈጠሩን ማረጋገጥ ነው።

እሴቶቹ ደግሞ ለትምህርትና ስልጠና ጥራት ቅድሚያ መስጠት፣ የሙያ ስነምግባር፣ የላቀ ምዘና፣ በጋራ መስራት፣ በዕውቀትና በእምነት መስራት፣ ተጠያቂነት፣ ለሕግ መገዛትና የላቀ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ናቸው። መምህራን በሚያስተምሩበት የትምህርት ዓይነት የተሻለ እውቀት ኖሯቸው ብቁ ተማሪዎችን እንዲያፈሩ የሚያግዘው የመምህራን ስልጠና በዘንድሮው ክረምት እንደሚጀመር የተናገሩት የዛሬው እንግዳችን ወ/ሮ አሰገደች ምሬሳም በሰጡን ማብራሪያ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ያጠናከሯቸው እነዚህኑ ነው።

በዘንድሮው ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ50 ሺህ መምህራን ልዩ የክረምት ስልጠና ለመስጠት፤ አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁን ትምህርት ሚኒስቴር ማስታወቁ ይታወቃል። ይህ የተገለጸው የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሀኑ ነጋ የ2016 ዓ.ም. የሁለተኛው ሩብ አመት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በየካቲት 26 ቀን 2016 ዓ፨ም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ባቀረቡት ሪፖርት ሲሆን፤ ስልጠናው የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን አቅም ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ መሆኑንም በሚኒስትሩ ተገልጿል።

በሪፖርቱ የአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ እና ትግበራ የደረሰበት ደረጃ የተገለጸ ሲሆን፤ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ለትምህርት ቤት አመራሮች እና መምህራን ስለሚሰጡ ስልጠናዎች ማብራሪያ መቅረቡ ይታወሳል። ባሉበት ሁኔታ ጥሩ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ስልጠና በመጪዎቹ ሐምሌ እና ነሐሴ ወራት እንደሚሰጥ የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ ስልጠናውም በሥራ ላይ ላሉ መምህራን በልዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናነት የሚሰጥ ሲሆን፤ ስልጠናው መምህራን ባሉበት የትምህርት ደረጃ እና በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ስነ-ዘዴ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህንን ልዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና በተመለከተ ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት በሚያስችል መልክ ከሚመለከታቸው የሥራው ኃላፊ ጋር ቆይታ ያደረግን ሲሆን፤ እንግዳችን የመምህራን እና የትምህርት ልማት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገደች ምሬሳ የሚከተለውን መረጃ አካፍለውናል።

እነዚህን ስልጠናዎች ለማከናወን የሚያስችሉ ሞጁሎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ሌሎች አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን እያደረገ መሆኑን የዴስክ ኃላፊዋ ወይዘሮ አሰገደች ምሬሳ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቆይታ የገለጹ ሲሆን፤ በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚሰጥ የተነገረለት ይህ ስልጠና ይበልጡኑ ትኩረት የሚያደርገው፤ የሁለተኛ ደረጃ የሂሳብ፣ የሳይንስ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች ላይ መሆኑንም ኃላፊዋ አስረድተዋል።

አቅም ማጎልበቻ ስልጠናው የመምህራንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን በማሰብም፤ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የተዘጋጀ መጠየቅ ተበትኖ፣ ተሰብስቦና ተተንትኖ በተገኘው ውጤት መሰረት የተዘጋጀ መሆኑን የሚናገሩት ኃላፊዋ፤ ይህ ብቻም ሳይሆን በርካታ የጥናትና ምርምር ስራዎችም የተሰሩ መሆናቸውን ይናገራሉ።

እነዚህ ስልጠናውን የሚወስዱት መምህራንና የትምህርት አመራር ባለሙያዎች በወሰዱት ስልጠና ልክ በትምህርት ስራው ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ሀገር ተረካቢ ተማሪዎቻቸውን ያበቃሉ። የተሻለ ትውልድ የመፍጠሩን ሰፊ ሥራ ይበልጥ ያጠናክራሉ ተብሎ እንደሚታሰብ የሚናገሩት የዴስክ ኃላፊዋ፤ ከአንድ መምህር ጀርባ ቢያንስ 300 ተማሪዎች መኖራቸውን፤ ከሦስት መቶ ተማሪዎች ጀርባ በሺዎች የሚቆጠሩ ወላጆች፤ ከወላጆችም ጀርባ ሀገርና ሕዝብ መኖሩን ማሰብ እንደሚያስፈልግም የተናገሩ ሲሆን፤ ስልጠናው በዛ ልክ ለውጥና መሻሻልን ያመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅም አስረድረዋል። በአጋዥ መጻሕፍት (ሞጁሎች) መታገዙም ሆነ ለወደፊት አሰራር ያመች ዘንድ የተለያዩ መመሪያዎች፣ ደንቦች ወዘተ ተዘጋጅተው ወደ ተግባር መሸጋገሪያ ወቅት ላይ መገኘታቸውም የትምህርት ሥርዓት ለውጡን ውጤታማ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

እንደ ዴስክ ኃላፊዋ ገለጻ በሀገራችን ከሚገኙት 800 ሺህ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች (የመንግሥት) ከ94 በመቶ በላይ የሆኑት ተገቢው የትምህርት ደረጃ (ማስረጃ) ያላቸውና የሚሰሩበትን የስራ ዘርፍ/መደብ/ የሚመጥን ነው። ይሁን እንጂ ብቃትን ለማረጋገጥ በተደረገ የዳሰሳ ጥናትም ሆነ የተማሪዎች የፈተና ውጤት (በተለይ ባለፈው አመት የተመዘገበው የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት) የሚያሳየው በሙያው የሚፈለገውን የትምህርት ደረጃና ማስረጃ ይያዙ እንጂ የአቅም ክፍተት መኖሩን ነው። በተለይ በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ሳይቀር ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ ታይቷል፤ በጥናትም ተረጋግጧል። በመሆኑም ይህ ልዩ ስልጠና አስፈልጓል።

ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞቻችንን በተመለከተም ያለባቸው ኃላፊነት በዴስክ ኃላፊዋ የተነሳ ሲሆን፤ እርሳቸው እንዳብራሩት በሀገራችን 28 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን ያሰለጥናሉ። ያሉት መምህራኖቻችንም ከእነዚሁ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የወጡ ናቸው። አሟልተዋል ተብለው ወደ ሥራ የተሰማሩ ናቸው። ውጤቱ ግን የተጠበቀውን ያህል ሆኖ አልተገኘም።

የሁሉም ትምህርት ተቋማት የትምህርት አሰጣጥና ፋሲሊቲ እኩል አይደለም። የጊዜ አጠቃቀማቸውም ሆነ የማስተማር ስነ ዘዴያቸው የተለያየ ነው። በአመራር በኩልም እንደዛው። በመሆኑም ወደ አንድና የተሻለ አሰራርና አሰለጣጠን መምጣት አለባቸው ያሉት ኃላፊዋ፤ አሁንም የምናሰለጥነው በእነዚሁ ዩኒቨርሲቲዎች ነው፤ ሌላ ተቋም የለንም፤ የትም ወስደን ልናሰለጥናቸው አንችልም። ያሉችን እቺው ሀገር ስለሆነች እዚሁ ነው ማሰልጠን የምንችለው። በመሆኑም መምህራኖቻችንን የሚያሰለጥኑት ተቋማት ብቁ ሆነው፤ የተሻለ የሰው ኃይል ለማውጣት ዝግጁ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል። ራሳቸውን ማብቃት ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ነው በኃላፊነት ላይ የተመሰረተ አስተያየታቸውን የሰጡት።

በስልጠናው የሚካተቱ መምህራንን በተመለከተም ጠይቀናቸው "በዚህ ዙር ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ነው እድሉን የሰጠነው። እንደ አጠቃላይ ግን ሁሉም መምህራን በሂደት ይህንን ልዩ ስልጠና የመሰልጠን እድል ያገኛሉ፤ የስልጠናው ተጠቃሚም ይሆናሉ ብለን ነው ያቀድነው። በተለይ በጥናት ላይ የተመሰረተው ይህ ልዩ ስልጠና የማስተማር ሥነዘዴ፣ ብቃት ማጎልበት እና መምህራኑ በሚያስተምሩበት ቴክስትቡክ (የማስተማሪያ መጻሕፍት) ላይ የተመሰረተ (የሚያተኩር) እንደ መሆኑ መጠን ሁሉም መምህራን የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግን ታሳቢ አድርጎ የተዘረጋ መርሀ-ግብር ነው" በማለት መልስ ሰጥተውናል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታየ ሀገራችን ከፍተኛ መምህራን አሏቸው ከሚባሉት ሀገራት የምትመደብ መሆኗን የሚናገሩት ወይዘሮ አሰገደች፤ ብቃት ላይ ግን ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች መኖራቸውን ያሰምሩበታል። "ከዚህ በፊት የብቃት ምዘና ተሰጥቷቸው ያንን፣ የሚያስተምሩትን ትምህርት መሰረት ያደረገ ፈተና ማለፍ የቻሉት መምህራን 24 በመቶ ብቻ ናቸው" ሲሉም የዚህን ስልጠና መነሻ እና መድረሻ፤ እንዲሁም የሌሎች ስልጠናዎችንም አስፈላጊነት ይገልፃሉ።

ለትምህርት ሥራ ዋና አስኳል የሆኑትን የትምህርት አመራሮችን፣ ማለትም ርዕሳነ መምህራን፣ ምክትል ርእስ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሚባሉትን የሚያካትተው ይህ ልዩ ስልጠና፣ መምህራንን ብቻም ሳይሆን ከ29 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎቻችንንም ያሰበ መሆኑን የሚናገሩት ዴስክ ሀላፊዋ፣ የመምህራን ብቃት ከሌለ ውጤታማ ተማሪ ሊኖር እንደ ማይችልና ተማሪዎች የመምህራኖቻቸው ፍሬዎች መሆናቸውንም ይገልፃሉ።

ከዚሁ ከስልጠና ጋር በተያያዘ በየዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በክረምት ኮርስ (ሰመር ፕሮግራም) ሲከታተሉ የነበሩ፣ ነገር ግን "ድንገት" (ያቋረጡት መምህራን እንደሚሉት) እንዲያቋርጡ የተደረጉትን በተመለከተም ጠይቀናቸው ነበር፤ እሳቸው እንደሚሉት ፕሮግራሙ የአመራር ክፍተት የታየበት፣ ወጥነት የሌለው፣ ግማሹ በሁለት ወር፣ ግማሹ በሁለት ዓመት፤ ያሰኘው ደግሞ ባሰኘው ጊዜ የሚያስመርቁበት፤ የተዘበራረቀና መምህራን ተመልሰው የትምህርት ጥራትን ሊያመጡ በሚችሉበት አይነት ዝግጅት አልነበረም እየተካሄደ የነበረው። በመሆኑም፣ ጥናት ተደርጎ በጥናቱ ግኝት መሰረት ለጊዜው እንዲቆም ተደርጓል።

በፕሮግራሙ 8ሺህ አካባቢ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢኤ) እና 34ሺህ አካባቢ ሁለተኛ ዲግሪ (ኤምኤ) መርሀ ግብሮችን የሚከታተሉ መምህራን ነበሩ። አካሄዱ የተሳሳተ ነገር ስላለው ተቋርጧል ያሉት ኃላፊዋ "ይቀጥላሉ?" ወይስ ፨ ፨ ፨" ላልናቸውም "አዎ፤ ይቀጥላሉ" በማለት መልሰውልናል።

በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ ብለናቸውም "ትምህርት ማህበራዊ ጉዳይ ነው። ባለቤቱም ማህበረሰቡ ነው። በመሆኑም ለትምህርት ጥራት መጠበቅም ሆነ አለመጠበቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁሉም ኃላፊነት አለበት። በተለይ ባለ ድርሻ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች ቀጥተኛ ተሳታፊዎች በመሆናቸው እየተከናወነ ካለው የትምህርት ሥርዓት ለውጡ ጎን ሊቆሙ ይገባል። በትምህርት ላይ የሚሰሩ ተቋማትም ከእኛ (ትምህርት ሚኒስቴር) ያልተናነሰ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ አብረን በጋራ ልንሰራ ይገባል" ብለዋል።

# ወቅታዊ

# ‹‹የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ የፀጥታ ሥራው ከሰዎች አልፎ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚታገዝ ይሆናል››

**-አቶ ጌታሁን አበራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ም/ ቢሮ ኃላፊ**

**እፀገነት አክሊሉ**



አዲስ አበባ ከተማን በሕዝብ ተሳትፎና ባለቤትነት ሰላምና ፀጥታ የሰፈነባት፤ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት ለኑሮ፣ ለሥራ እና ለመዝናኛ ተመራጭ የሆነች ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በተለይም ከተማዋ ሰላምና ፀጥታዋ የተረጋገጠ ይሆን ዘንድም በብዙ እየተለፋ ይገኛል። ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ከሚወጡ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ካሉ ተቋማት መካከል ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ አንዱ ነው።

አቶ ጌታሁን አበራም በቢሮው የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ናቸው። አቶ ጌታሁን ወደዚህ ተቋም ከመምጣታቸው በፊት በተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ ያገለገሉ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል በክፍለ ከተማ ደረጃ የፍትህ ጽህፈት ቤት አቃቤ ሕግ፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሰላምና ጸጥታ ጽህፈት ቤት በኃላፊነት የሠሩ ሲሆን፤ በቼሻየር ፋውንዴሽን ውስጥም የድርጅቱ የፕሮግራም አስተባባሪ በመሆን አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአዲስ አበባን የጸጥታ ሁኔታ በመምራት ላይ ይገኛሉ። እኛም የአዲስ አበባን ሰላምና ጸጥታ በተመለከተ ከአቶ ጌታሁን አበራ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነቱ ምንድን ነው? ከሚለው እንጀምር**

**አቶ ጌታሁን፡-** ቢሮው በአዋጅ 74 /2014 የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አለ፤በዚህ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ቢሮው የከተማዋን ሰላም ደህንነት ማስጠበቅ አንዱ ኃላፊነቱ ሲሆን፤ ሕዝቡን በጸጥታ ጉዳይ ላይ ማሳተፍ ደግሞ ሌላው ተግባርና ኃላፊነቱ ነው። በዚህም ሕዝቡን ማወያየት፤ ማደራጀት የሰላም ባለቤት ራሱ እንዲሆን የማቀናጀት ሥራንም እንሠራለን።

በሕጉ ላይ እንደተቀመጠው የከተማዋን ሰላም እንዲጠበቅ ማድረግ ሰዎች በሰላም ሰርተው፣ ተምረው፣ ነግደው እንዲገቡ ማስቻል በጠቅላላው ከተማዋ ከየትኛውም አዋኪ ነገር ወጥታ ሰላሟ የተረጋገጠ ለመኖሪያ ምቹ የሆነች እንድትሆን ማስቻል ይጠቀሳል።

በሌላ በኩልም በፀጥታ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና የፀጥታ አማካሪ ሆኖ ይሠራል፤ ለፀጥታና ሰላም አስጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተገቢ የሆነ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንደ አግባብነቱ ራሱ ወይም ከሚመለከተው አካላት ጋር በመቀናጀት የእርምት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል።

የግጭት መንስዔዎችን በጥናት ይለያል፣ ግጭት እንዳይከሰት ይከላከላል፤ ሲከሰትም ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ይፈታል፤ በከተማው ልዩ ልዩ ሃይማኖትና ቤተ-እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸው የፌዴራልም ሆነ የከተማው አስተዳደር አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

እነዚህ ሥራዎች እየተሠሩም ኅብረተሰቡን በየሚያውኩ ጉዳዮች ሲከሰቱም በሕግ አግባብ ሥርዓትን የማስያዝ በዚህ ደግሞ ለነዋሪው ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ሥራን ይሠራል። ከዚህም በተጨማሪ እንደ ትምህርት ተቋማት፣ የእምነት ተቋማትና ሌሎችም የሚሰጡት አገልግሎት ሰላማዊና ደህንነቱ የተጠበቀ ይሆን ዘንድ አዋኪ ድርጊቶችን የማስቀረትና የማረም ተግባራት ይሰራሉ።

በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት፣ በነዋሪው ደኅንነት፣ ሰላም እና ፀጥታ አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ አግባብነት ካላቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር እና ሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤ እንደ አግባብነቱ ችግሮችን በተናጠል ወይም በጋራ የመፍታቱን ሥራ እየሠራ ይገኛል ።

በሌላ በኩልም የቢሮ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በስውር የነዋሪውንና የመንግሥትን ጥቅም ጉዳት ላይ ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ነዋሪውንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ይከላከላል።

ከፀጥታ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታ እና አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ እንዳግባብነቱ ራሱ ወይም በተጠሪ ተቋምና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቅሬታዎቹና አቤቱታዎቹ መልስ እንዲያገኙ ያደርጋል። ለሕግ አስከባሪ አካላት እና ለነዋሪዎች በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የሕዝብ አገልጋይነት ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንዲሁም ከሰላም እጦት ስጋት ነጻ እንድትሆን የምትሠሩት ሥራ ምን መልክ አለው?**

**አቶ ጌታሁን፡-** በበጀት ዓመቱ ከያዝነው እቅድ ዋነኛው ኅብረተሰቡን የሰላም ባለቤት ማድረግ ነው። ይህ ማለት እንግዲህ ሰፊ እቅድ ነው። መዲናዋ ትክክለኛ ነው ብሎ ማለት ባያስደፍርም ከ6 ሚሊዮን የማያንስ ሕዝብ ይኖራል ተብሎ ነው የሚታሰበው። ይህንን ነዋሪ የሰላም ባለቤት ማድረግ ሲባል በከተማዋ ላይ እየተከናወኑ ያሉ ወቅታዊ ጉዳዮችን ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግ አንዱ በመሆኑ ይህንንም ሥራ የምንሠራው በተለያዩ ጊዜያት መድረክ እየፈጠርን በማወያየት ነባራዊውን ሁኔታ በማስገንዘብ ነው።

እንደ ከተማ አብዛኛው ነዋሪ ጋር መድረስ ፀጥታን ለማስከበር አይነተኛ መንገድ በመሆኑ ኅብረተሰቡን በሴቶች፣ በወጣቶች እንዲሁም መላ ነዋሪውን በማለት እየተከፋፈለም ሳይቋረጥ የሚሠራ ሥራ ነው። እስከ አሁን ባለው ሁኔታም በተሳካ ሁኔታ እየተሠራበት ያለ ሂደት ነው።

ከዚህ የሚቀጥለው ሕዝቡን ማደራጀት ሲሆን፤ ይህም በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተጀመረውና ኅብረተሰቡ በራሱ ፍቃደኝነት የሰላም ሠራዊት ሆኖ በምሽት እየወጣ አካባቢውን የሚጠብቅበት ሂደት ነው። እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳን ከክፍያ ነጻ ሆነው በሙሉ ፍቃደኝነት አካባቢያቸውን እየጠበቁ ቢሆንም የሚተዳደሩበት ሕግና ሥርዓት ደግሞ አለ። ስልጠናም ያገኛሉ። ከስልጠናው ባሻገር በጎ ፈቃደኛ የሰላም ሠራዊቶችን በሥራው ላይ መሠማራታቸውን የሚገልጽ መለያ ተዘጋጅቶላቸው የፀጥታ መዋቅሩ ጋር ተቀናጅተው በመስራት ላይ ናቸው። ይህ ደግሞ የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ከምናረጋግጥባቸው መንገዶች መካከል ተጠቃሹ ነው።

በዚህ ሥራው ኅብረተሰቡ በአካባቢ ፤በመንደሩ ያለውን ጠቅላላ የፀጥታ ሁኔታ ከማረጋገጡም በላይ ለከተማዋ የፀጥታ ቢሮ ቀኝ እጅ በመሆን መረጃን ከመስጠት ጀምሮ የተለያዩ እገዛዎችን እያደረጉ ነው።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ይህ የሰላም ሠራዊት ሁሉን የሚመለከት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በተለይም የገንዘብ አቅማቸው ጥሩ የሆኑ ሰዎች የአካባቢ ጥበቃዎችን በገንዘባቸው እየቀጠሩ እኛም አስፈላጊውን ስልጠና እየሰጠን ከማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ጋር ተቀናጅቶ የጥበቃ ሥርዓቱ እየተከናወነ ነው። ከዚህ አንጻር ገንዘብ የሌለው በጉልበቱ ገንዘብ ያለው ደግሞ በገንዘቡ ለሰላምና ፀጥታው የበኩሉን አስተዋጽኦ እየተወጣ ነው ማለት ይቻላል ።

በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም ቁጥራቸው 833 ገደማ የሚደርሱ ማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ ማእከላት አሉ። እነዚህ ተቋማት ደግሞ የፖሊስን አገልግሎት በየአካባቢው ተደራሽ ለማድረግ በተለይም ግጭቶች ሲኖሩ እንዲፈቱ በማድረግ አዋኪ ተግባራትም ከብሎኮች ሳይወጡ የሚፈቱበት መፍትሔ የሚሰጡ ናቸው። በመሆኑም የሕዝቡ ተሳትፎ ማሳለጫ ናቸው ማለት ይቻላል። ሕዝቡም እኔም ለአካባቢዬ ዘብ እቆማለሁ ብሎ ተሳትፎውን በማሳየት ላይ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- የኅብረተሰቡ ተሳትፎ በዚህ መልኩ ከታየ የፀጥታ አካላትስ የከተማዋን ሰላም በቅንጅትም ይሁን በተናጠል በተገቢው ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚሠሩት ሥራ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጌታሁን፡-** አዎ የፀጥታ መዋቅሩ ማለትም የከተማው ፖሊስ፣ሌሎች የፀጥታ ተቋም የከተማዋን ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ ሌት ተቀን ከመስራታቸውም ባሻገር ራሳቸውን በቴክኖሎጂ ለማዘመን የሚያደርገው ጥረት የሚያበረታታና ብዙ ውጤቶች የታዩበት ነው። ይህ የፀጥታ ኃይል ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀናጅቶ ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን በአዲስ አበባ ዙሪያ የሸገር ከተማ አስተዳደር ጋር በመቀናጀት በአምስቱም መውጪያና መግቢያ በሮች ላይ ያለውን የፀጥታ ሁኔታ አስተማማኝ ለማድረግ የቅንጅት ሥራውንም በሚገባ እየሠራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሰላምና ፀጥታ የማስከበር ሥራው ዘመን በወለዳቸው ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፍ በማድረጉ በኩል የተሰራው ሥራ ምን ይመስላል ?**

**አቶ ጌታሁን፡-** አዎ የፀጥታ ሥራውን የማዘመን ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራዎች እየሠራን ነው። ከተማዋ ውስጥ ለፀጥታና ደህንነት ሥራ ጠቃሚ የሆኑ የደኅንነት ካሜራዎች በተለያዩ ተቋማት ውስጥ እየተተከሉ ነው። በዚህም የደኅንነት ካሜራዎች በከተማዋ ዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ ከማድረጋችንም ባሻገር በከተማዋ ውስጥ የሚገነቡ ትልልቅ ሕንፃዎች ካሜራ እንዲገጠምላቸው እየተደረገ ነው። ይህ ደግሞ በሕንፃው ባለቤቶች የሚከናወን ሲሆን፤ የሕንፃቸውን ሥራ ደኅንነት ከመጠበቅም አልፎ ከውጭ ያለውን የፀጥታ ሥራ ለመከታተል ከፍ ያሎ አስተዋጽኦን እያበረከተ ነው።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹ የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ የፀጥታ ሥራው...

ከገጽ 9 የዞረ



ከዚህ ባሻገር ካሜራውን መትከል ብቻ ሳይሆን በአንድ ማዕከል ላይ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ሥራም እየተሠራ ነው። በቀጣይም የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ የፀጥታ ሥራው ከሰዎች አልፎ በሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ የሚሠራ ይሆናል። ይህ ደግሞ የፀጥታው ሥራ ስማርት ሆኖ እንዲቀጥል እንደሚያደርገው እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- እንግዲህ የፀጥታ ኃይሉ ከሕዝቡ አሁን ደግሞ ከሸገር ከተማ አስተዳደር ጋር በቅንጅት ሥራዎችን እየሠራ ስለመሆኑ ነግረውኛልና እንደው በዚህ ቅንጅታዊ አሠራር የመጡ ለውጦችን ማንሳት እንችል ይሆን?**

**አቶ ጌታሁን፡-** አዎ በሰላምና ጸጥታ ሥራ ላይ ቅንጅታዊ አሠራር ተኪ የለሽ ሚናን የሚጫወት ነው። ይህም በመሆኑ እኛም በልዩ ትኩረት የምንሠራው ሥራ ነው። ከዚህ አንጻር እስከ አሁን በተለይም ኅብረተሰቡንና ወጣቱን ወዳልተገባ መንገድ ይወስዱ የነበሩ እንደ ሺሻ ቤቶች፤ ቁማር መጫወቻዎች እንዲሁም ለሌሎች እኩይ ተግባራት ወጣቶችን የሚስቡና የሚሰበስቡ ቦታዎችን በጋራ በማሰስ ጥቆማዎችን በመቀበል ቤቶቹ እንዲዘጉ ንብረቶች እንዲወረሱ እና በሥራው ላይ የተሳተፉትም በሕግ እንዲጠየቁ በማድረግ አሁን ላይ ከተማዋ በአስተማማኝ ሰላም ላይ እንድትገኝ ማድረግ ተችሏል። ይህ ሥራም አንዴ ተከናውኖ የሚያበቃ ባለመሆኑ በየጊዜው ተከታታይነት ያለው ሥራ እየተሠራ ከተማዋን ወደተሻለ ደረጃ እያደረስን ነው ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጠቅላላው ግን ስናየው በተለይም በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየተከናወነ ያለው የሰላምና የፀጥታ ሥራው ውጤታማ ነው የታለመለትን ግብ መቷል ማለት እንችላለን?**

**አቶ ጌታሁን፡-** በነገራችን ላይ ከተማችንን ለማወክ ብዙ ዓይነት አስተሳሰቦች እየተንጸባረቁ ነው፤ እዚህም እዚያም ችግር ለመፍጠር ፍላጎቶች አሉ፤ ምናልባት አዲስ አበባ ላይ የሆነ ነገር ብንፈጥር በመላ ሀገሪቱ ላይ ችግር ለመፍጠር ይቀለናል ብለው የሚያስቡም ብዙ ናቸው። በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎችም ሙከራዎች ይደረጋሉ። እነዚህ ሙከራዎች ደግሞ የሚከሽፉትም ሆነ እየከሸፉ ያሉት በኅብረተሰቡ ተሳትፎ በሚሰሩ የሰላምና የፀጥታ ሥራዎች ነው። እኛም ውጤታማነታቸውን የምንለካው ከዚህ አንጻር ነው።

ይህንን በተጨባጭ ማሳየት ከተፈለገ በያዝነው ዓመት ብቻ ያከበርናቸውን የአደባባይ በዓላትና አንዳንድ ሁነቶችን ማንሳት በቂ ነው። ለምሳሌ የዘመን መለወጫ፣ እሬቻ፣ ደመራ፣ ጥምቀት አሁን ደግሞ በቅርቡ ኢድን ስናከብር በብዙ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ በጎዳናዎች ላይ ወጥቶ በዓሉን ተካፍሎ ያለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም ወደ ቤቱ ገብቷል።

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ በየቀኑ በርካታ ሰዎች ያለምንም ስጋት ከቦታ ቦታ ተዘዋውረውና ሠርተው በሰላም የሚገቡባት ከተማ ሆናለች።

አሁን ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረው ከተማን የማልማት የማዘመን የመለወጥ ሥራ አለና ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ ነገሮች ስለሚኖሩ እንደ ፀጥታ ቢሮ ይህንን የልማትና የለውጥ ሥራ የሚመጥን አገልግሎት እየሰጠን ነው። በየጊዜውም አሠራሮችን እየፈተሽን ክፍተቶችን እያስተካከልን እየሄድን ነው። 24 ሰዓት የሚሠራው የልማት ሥራ ያለምንም ሳንካ እየተሠራ ነው፤ሕዝቡም በሰላም ወጥቶ እየገባ ነው።

በከተማዋ የትምህርት ተቋማት አካባቢም ያሉ አዋኪ ነገሮች በራሱ ለይተን እርምጃ እንድንወስድ ከፍተኛውን እገዛ ያደረጉልን ከኅብረተሰቡ የተውጣጡ የሰላምና ፀጥታ አባላት ናቸው። እነሱ እገዛ ባያደርጉልንና እኛም በዛ ልክ እርምጃ መውሰድ ባንችል ኖሮ ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርታቸው እየወጡ አልባሌ ቦታዎች እየዋሉ የትምህርት ሥርዓቱ ይታወክ ነበር። በጠቅላላው እነዚህና ያልጠቀስኳቸውም

**በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ በየቀኑ በርካታ ሰዎች ያለምንም ስጋት ከቦታ ቦታ ተዘዋውረውና ሠርተው በሰላም የሚገቡባት ከተማ ሆናለች**

በርካታ የትብብር ሥራዎች በመኖራቸው ሥራው ውጤታማ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን ፡-አንዳንድ ጽንፈኛ ኃይሎች የከተማዋን ፀጥታ ለማወክ የተለያዩ ጥረቶችን ያደርጋሉ፤ሙከራዎችም ነበሩና እነዚህን ነገሮች እግር በእግር የመከታተሉ ሥራ ምን ይመስላል?**

**አቶ ጌታሁን ፡-** ጽንፈኝነት ትርጉሙ ሰፊ ነው። ጽንፍ የወጣ አስተሳሰብ ግለሰብ ቡድን ሁሉ ለውይይት በር አይሰጥም፤ በማህበረሰቡ ላይ ሃሳቡን በጉልበት በኃይል መጫን ነው የሚፈልገው፤መንግሥትን ማስገደድ ነው ህልሙ፤ ይህ ደግሞ አሁን ባለንበት ሥርዓት ሊሆን የማይቻል ነገር ነው። መንግሥት በምርጫ ተወዳድሮ ነው ስልጣን የያዘው ፤ስለዚህ ይህንን መንግሥት ከስልጣን አወርዳለሁ የሚል አካልም በምርጫ ተወዳድሮ ነው ማሸነፍና ስልጣን መያዝ ያለበት። በጉልበት በትጥቅ መንግሥትን ማንሳት አይቻልም።

ይህም ቢሆን ግን አሁን እየታዩ ያሉት አንዳንድ አዝማሚያዎች የሚያሳዩት መጥፎ ሁኔታ አለ። በተለያዩ ክልሎች ላይ ያሉ ጽንፈኝነቶችንም ወደከተማ ለማምጣት የሚደረጉ ጥረቶች ይስተዋላሉ፤ ነገር ግን እኛ እስከ መንደር ድረስ አደረጃጀትን የፈጠርን ከመሆኑ አንጻር የመረጃ ሥርዓቱ በእያንዳንዱ መንገድ እየተሰበሰበ ስለሚመጣ መረጃውንም መሠረት አድርገን ሕግ የማስከበር ሥራውን ስለምንሠራ ችግሩን በአጭሩ እንቀጨዋለን።

ይህም ቢሆን ግን የተለያዩ ሙከራዎች አይደረጉም ማለት አይቻልም። ለምሳሌ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችን ይዞ ወደከተማ ለመግባት መሞከር፣ እምነቶችን ሽፋን አድርጎ ለእኩይ አላማ መንቀሳቀስ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሽፋን አድርጎ መንቀሳቀስ አለ። ይህንንም እንደ ፀጥታ ቢሮ እግር በእግር እየተከታተልን ሕግ የማስከበር ሥራዎችን እንሠራለን።

በነገራችን ላይ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች አንግበው የተነሱትን አላማ በከተማዋ ላይ ለማራመድ የሚያደርጉትን ጥረት የከተማው ነዋሪ አይፈቅድም። ሰላሙን የሚያደፈርስ ነገርም አይቀበልም። ሕዝቡ በሰላም ወጥቶ ገብቶ ሠርቶ ሕይወቱን መቀየር ነው የሚፈልገው። ከዚህ አንጻር ሕዝብ ውስጥ ተሸሽጎ እኩይ ተግባርን አስፈጽማለሁ ማለት የሚቻል አይደለም።

በጠቅላላው ማንኛውም ጽንፈኛ ኃይል መሄጃውም መዳረሻውም አፍራሽ ነው፤ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ የሚጠቅም ነገር የለውም፤ ሃሳቡን ይዞ ለሚንቀሳቀሰው አካልም ጥቅሙ ምንም ነው፤ በዚህ አግባብ ከተማችን ውስጥ ያለውን ሁለንተናዊ ሰላም እያረጋገጥን የምንሄድ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ቢሮ በከተማ ደረጃ ሰላምና ፀጥታን በማስከበር ሂደቱ ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው ? ከማንስ ምን ዓይነት እገዛን ትፈልጋላችሁ?**

**አቶ ጌታሁን፡-** ሕዝቡ ሰላም ወዳድ ነው፤ ለሰላም የሚሰጠው ግምት ከፍተኛ ነው፤ እኛም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሥንሠራ የምንለው ነገር ሰላም ያለው በእጃችሁ ነው፤ አንዳንድ ግለሰቦች ይህንን ሰላማችሁን ሊነጥቋችሁ ያስባሉ፤በመሆኑም ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ ብለን እናስተምራለን።

በነገራችን ላይ አንዳንድ ሰዎች ከራሳቸው ጋር በሃሳብ ይጋጫሉ፤ ይህንን ሁኔታ ይዘው ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ችግር ይፈጥራሉ፤ ይህም ከፍ እያለ ሄዶ ወደማህበረሰብ ይደርሳል በመሆኑም ሰዎች መጀመሪያ ሊያረጋጉ የሚገባቸው ራሳቸውን ነው፤ ይህ ሲሆን በእጃቸው ያለውን ሰላም መጠበቅ ይጀምራሉ ሌሎችንም ከመረበሽ ይቆጠባሉ።

እንደ እኛ ሥራ ግን ፈታኝ እየሆነብን ያለው ነገር ከማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ጋር ያለው ጉዳይ ነው። ማህበራዊ ሚዲያ ለበጎ ነገር ከተጠቀምንበት ብዙ የሚያሠራ የመሆኑን ያህል ባልተገባ ሁኔታ የሚጠቀሙበት አካላት ግን ማህበረሰቡ ላይ የሌለ ነገር በመፍጠር ጫና እንዲያድርበት ያደርጋል።

የሰላምና የደኅንነት ጉዳይ የመንግሥት ሥራ ብቻ አይደለም ሕዝቡ በተለይም የመገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ የሆነ ትግል ማድረግ አለባቸው። ሚዲያው እውነትን ከሃሰት እየለየ እያወገዘ ትክክለኛውን መረጃ ለማህበረሰቡ የሚያደርስበት አሰራር መከተል አለበት።

በሌላ በኩል ኅብረተሰቡ የከተማው ፀጥታ ባለቤት እንደመሆኑ ጎረቤቱ ማን እንዳለ ምን እንደሚሠራ በተቻለ መጠን ማወቅ ይኖርበታል። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ቤት፤ ሕንፃ ፤መኪና የሚያከራዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተከራያቸውን ማንነት ማወቅ ለምን አገልግሎት ሊውል እንደተፈለገ መረዳት አለባቸው። በተጨማሪም መኪናም ሆነ ቤት አከራይተው የሚኖሩ ሰዎች የተከራዮቻቸውን ማንነት የሚገልጽ በቂ መረጃን እስካላገኙ ድረስ ንብረታቸውን አሳልፈው ባለመስጠት መተባበር ይገባቸዋል።

ያለችን አንድ ሀገር ናት ሀገራችን ችግር ገጠማት ማለት መግቢያ መሸሸጊያ አጣን ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሱዳንን በመሳሰሉ ጎረቤቶቻችን ላይ እየተፈጠረ ባለው ነገር ብቻ ማየት በቂ ይመስለኛል። በመሆኑም ችግር ፈጣሪዎችን ተባብረን አይሆንም በማለት ሁላችንም የከተማችን የሀገራችን ሰላም ይመለከተናል ብለን ልንነሳ የግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የፀጥታ ኃይሉ ሥራዎችን የሚደግፍበት መንገድ ምን ይመስላል?**

**አቶ ጌታሁ፡-** የልማት ሥራው ከተማችንን ከማዘመን፣ ከማበልጸግ እንዲሁም ከተማውን ከሌሎች የዓለም ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ ከማድረግ አንጻር እየተሠራ ያለ ሥራ ነው። በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ከተማ የነዋሪዎቿ ብቻ ሳትሆን በዓለም የዲፕሎማቲክ መቀመጫ ሀገራት መካከል ሦስተኛዋ ከተማ ናት፤ከዚህ አንጻር ልማቱ ያንን የሚመጥን መሆን አለበት በማለት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ኅብረተሰቡም ይህንን በመረዳትና የመንግሥትን ሃሳብ በሙሉ ልብ በመቀበል ሥራውን እየደገፈ ነው ያለው፤ በልማት የሚነሱ አካባቢዎችም ይነሱ ሲባል ሕዝቡ እየተባበረ ነው ።መንግሥትም ቢያንስ ይኖሩ ከነበረው ኑሮ ሻል ወዳለ ኑሮ የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ እያመቻቸም ስለመሆኑ መናገር ይቻላል።

ለምሳሌ እዚህ ፊትለፊታችን ያለው የዶሮ ማነቂያ አካባቢ ምን እንደነበር ይታወቃል። በጣም የደከሙ ቤቶችን የያዘ፤ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በተገቢው ሁኔታ መስጠት የማይቻልበት ፣ በፀጥታው አንጻርም በርካታ አዋኪ ነገሮች በየቀኑ የሚፈጠሩበት አካባቢም ነበር፤ አሁን ከዚህ አካባቢ የተነሱ ሰዎች የተሻለ መኖሪያ አግኝተው መኖር እንዲችሉ እየተደረገ ነው።

ይህ ሁሉ ጥሩ ነገር ነው እኛም በፀጥታው ያለውን ሥራ በሚገባ እየሠራን በአንዳንድ ማህበራዊ ገጾች ላይ የሚለቀቁ እኩይ ተግባራትን የሚያስተላልፏቸውን የተዛቡ መረጃዎች ለማስተካከል በተጠናከረ የፀጥታ መዋቅር ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጌታሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የፋሽን ዲዛይነሯ የሰው ኃይል ልማት ግብ ማሳኪያው ተቋም

**በኃይሉ አበራ**

ኢትዮጵያ ውስጥ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ለፋሽን ዘርፍ መልካም እድሎችን ይዞ መጥቷል።በኢንዱስትሪ ፓርኮችና ከፓርኮቹ ውጪ ሆነው የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ባህላዊና ዘመናዊ የጨርቃጨርቅ አልባሳት የሚያመርቱ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያዎች እያቀረቡ ያሉበት እንዲሁም የፋሽን ትርኢቶች እየተበራከቱ የመጡበት ሁኔታ የሚያስገነዝበውም ይህንኑ ነው።

ዜጎች በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተውም በግልም ከሚሰማሩባቸው ዘርፎች መካከል ለፋሽን ዘርፍ ከፍተኛ ቅርበት ያለው የጋርመንት ኢንዱስትሪ ነው። የጋርመንት ኢንዱስትሪው እየተስፋፋ ከመሆኑም በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሀገሪቱ የፋሽን ትርኢቶች በስፋት መታየት ጀምረዋል። በፋሽን ኢንዱስትሪ ላይ ስልጠና የሚሰጡ እንዲሁም የሚያስተምሩ ተቋማት ቁጥርም እየጨመረ መሆኑ ይገለጻል።

ኑሯቸውን በጣሊያን ያደረጉት «ዳማሪዮስ ፋሽን እና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት» በሚል በአዲስ አበባ የፋሽንና ቴክኖሎጂ ተቋም የመሰረቱት ወይዘሮ ሰናይት ማሪዮም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የፋሽን ኢንዱስትሪ እያደገ መሆኑን መስክረዋል። መንግሥት ለጋርመንት ኢንዱስትሪው የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተከትሎ በርካታ የጋርመንት ፋብሪካዎች ወደ ሀገሪቱ እየገቡ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ የተወለዱት ወይዘሮ ሰናይት ማሪዮ በፋሽን ዲዛይን ሙያቸው ይታወቃሉ።በአፍሪካ ደረጃ በደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ግብፅ፤ እንዲሁም በኒውዮርክ፣ ፓሪስ፣ ሚላን በነበሩ የዓለም አቀፍ መድረኮች በፋሽን ስራዎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የፋሽን ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ሁኔታ ተለውጧል የሚሉት ወይዘሮ ሰናይት፣ ያለንበት ዘመን የብራንዶች እና የኢ-ኮሜርስ ዘመን ነው ። በየጊዜው እያደገ ያለውን ይህን ኢንዱስትሪ ለማጠናከር ጥራት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ያስፈልጋል ሲሉም ያስገነዝባሉ።

በከተማ ብቻ ሳይሆን ስለፋሽን ምንም እውቀት በሌለባቸው የገጠር አካባቢዎች እንዲሁም ሀብቱ ባለባቸው አካባቢዎች በርካታ የፋሽን ትርኢቶች ማዘጋጀታቸውን ወይዘሮ ሰናይት ያስታውሳሉ። ይህንም ሲያስረዱ የጉራጌ ብሔረሰብን ባህል ለአብነት ጠቅሰዋል። የብሔረሰቡን ባህል በፋሽን ለማስተዋወቅ የሚቻልበትን ፋሽን ሾው አዘጋጅተው እንደነበርም ገልጸዋል።

ማህበረሰቡ በስፋት የእንሰት ውጤቶችን እንደሚመገብ ጠቅሰው፤ ከእንሰት ተዋፅዖ አንዱ በሆነው በቃጫ ደግሞ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተለያዩ አልባሳትን መስራት እንደሚቻል ገልጸዋል። በዚህ እንሰት ከምግብነትም አልፎ ለአካባቢው ኢኮኖሚ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ጠቅሰው፣ በአካባቢያችን ያሉንን ሀብቶች በመጠቀም እንዴት ወደ እድገት መምጣት እንደሚቻል በማሳየት፤ ለወጣቶች በስራ ፈጣሪነት እንዲነቃቁ መድረኮችን መፍጠራቸውን ተናግረዋል።

እሳቸው በሚያዘጋጁቸው የፋሽን ትርዒቶች ጀማሪ ዲዛይነሮችን እና ልምድ ያላቸውን አብረው እንዲሰሩ እና ልምድ እንዲቀስሙ አድርገዋል። በዚህም ብዙ ሞዴሎችን እና ዲዛይነሮችን በማፍራት በዘርፉ ላይ የራሳቸውን አሻራ እንዲያሳርፉ አስተዋፅኦ እያበረከቱ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ለረጅም ዓመታት በጣሊያን ሀገር አድርገው የቆዩት ወይዘሮ ሰናይት፣ አሁን ደግሞ ወደ ሀገራቸው በመመለስ በኢትዮጵያ ደረጃውን የጠበቀ የፋሽን ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ከተማ በ1600 ካሬ ሜትር ቦታ በመመሥረት ላይ ናቸው።

ወይዘሮ ሰናይት፤ በኢትዮጵያ ለታዳጊ ንድፍ ባለሙያዎች(ዲዛይነሮች) መድረኮችን የሚያቀርቡ በርካታ ዓለም አቀፍ የፋሽን ሳምንታት እንዳሉም ይጠቅሳሉ፤ «ኢንስቲትዩቱ ተማሪዎቻችን እነዚህን መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ይሰራል» ይላሉ፤ ይህም በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለኢትዮጵያውያን የፋሽን ባለሙያዎች ብሩህ ተስፋ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጋርመንት ፋብሪካዎች የሚቀጠር በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚፈለገውን ያህል እንዳልነበረ ጠቅሰው፣ በሀገሪቱ ውስጥ የፋሽን ኢንዱስትሪ ማሰልጠኛዎች ብዙም እንዳልነበሩም ይገልጻሉ።በፋሽን ዲዛይን ልዩ ኮርሶችን የሚሰጡ ፕሮፌሽናል ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ጥቂት በመሆኑ በሰለጠኑ ዲዛይነሮች አቅርቦት ላይ ያለውን ትልቅ ክፍተት ለመሙላት የእሳቸው ተቋም የጎላ ድርሻ እንዳለው አስታውቀዋል።


ፋሽን ዲዛይነር ሰናይት ማሪዮ

የፋሽን ትምህርት ቤቶችን መክፈትና በዘርፉም ስልጠናን መስጠት የቀጣዩን ትውልድ ተሰጥኦ ማሳደግ ያስፈልጋል የሚሉት ዲዛይነሯ፣ በፋሽን ዲዛይን፣ ንግድ እና ቴክኖሎጂ መደበኛ ትምህርት ለመስጠት ያተኮሩ ተቋማት እና ውጥኖች የአገራችንን ፋሽን ደረጃዎች ዓለም አቀፋዊ መመዘኛዎችን ለማሟላት ወሳኝ ናቸው ብለዋል። በተቋማቸው የተማረ የሰው ሃይል የፋሽን ኢንዱስትሪውን ዘላቂነት እና ቀጣይ ፈጠራን በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት አስታውቀዋል።

እሳቸው ከመንግሥት ተቋማት በተጨማሪ ሰዎች በተግባር እየሰሩ መማር የሚችሉባቸው የግል ትምህርት ቤቶች መቋቋም እንዳለባቸው በማመን ጥናት አድርገውም ተቋም ወደ መክፈት ስራ ማግባታቸውን ይናገራሉ።በጥናቱ በርካታ ትምህርት ቤቶችም በቦታ ጥበት ይቸገሩ እንደነበር ያመላክታሉ።ይህን ሁሉ በመገንዘብ ነው ራሱን የቻለ ፋሽን እና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም ወደ ተግባር እንደገቡ ያስረዳሉ።

ትምህርት ቤቱ ከሌሎች የፋሽን ትምህርት ቤቶች ልዩ የሚያደርጉት ሁኔታዎችም አሉት። ከእነዚህም መካከል አንዱ ስልጠናውን በሚገባ ላጠናቀቁ ተማሪዎች በፋሽኑ ስመ ጥር ወደ ሆኑ ሀገራት በመላክ ታዋቂ በሆኑ የፋሽን ስቱዲዮ እና ተቋማት ውስጥ የተግባር ልምድ እና ልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበትን እድል ተመቻችቷል።

ተቋሙ በአጫጭር ስልጠናዎች ሥራውን በመጀመር ዲፕሎማ እና ዲግሪ ድረስ በአጭር ጊዜ ለማሳደግ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።ከመስከረም ወር በኋላም አዲስ ፈቃድ በማውጣት እስከ ዩኒቨርሲቲ ለማሳደግ መታሰቡንም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ታዋቂ ከሆኑ የፋሽን ዲዛይነሮች ጋር በመተባበር ተማሪዎች ስራዎችን የሚያሳዩበት አመታዊ የፋሽን ሾው ከማዘጋጀት እና የገበያ ትስስር ከመፍጠርም ባለፈ ስራ አጥነትን ለማስወገድ አሰሪዎችን እና ተመራቂዎችን የሚገናኙበት እድል ይፈጥራል።

ኢትዮጵያ ፋሽን እና የፈጠራ ስራ ዘርፍን በማበረታታት ወደ አለም አቀፍ ላኪነት በመቀየር ሁሉን አቀፍ የእድገት ተምሳሌት ሆና ማገልገል ትችላለች ሲሉ ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ በ20 ሚሊዮን ብር ካፒታል የተቋቋመ መሆኑን ጠቅሰው፣ መሠረታዊ ከሆነ ልብስ ለክቶ፣ ቆርጦ፣ ከመስፋት ጀምሮ እስከቅንጡ የፋሽን አስተዳደሮች፣ የጌጣጌጦች ዲዛይን፣ የኮምፒውተር ኮዲንግ እና ፕሮግራሚንግ፣ ግራፊክ ዲዛይን ስራዎች የሚሰጡበት መሆኑን ጠቁመዋል። ተቋሙም የፋሽንን ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ጋርመንት ወደ መክፈት በኢንዱስትሪ ደረጃ ጨርቃጨርቅ ወደ ማምረት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የባከነው የአባቶች እውቀት

**ዋስልኝ አየለ**

ታክሲ ውስጥ ወይም በሆነ መገልገያ ቦታ ውስጥ አጋጥሟችሁ ሊሆን ይችላል። በዕድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች በትንሽ ትልቁ ይገረማሉ። በሆነ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠት ይወዳሉ። አድማጩ ወጣት ከሆነ በይሉኝታ ይሰማቸዋል እንጂ በውስጡ «አይ የሽማግሌ ነገር!» እያለ እንደተንዛዙበት አድርጎ ይቆጥረዋል፤ በትህትና ለመማር ብለው የሚያዳምጡት እንዳሉ ሆነው ማለቴ ነው። ምክንያቱም ወጣቱ በብዙ ነገር የተወጠረ ነው፤ ቀልቡ በአጫጭር ነገሮች የተላመደ ነው። አዛውንቱ ደግሞ የውስጣቸውን የሚተነፍሱበት ዕድል ብዙም ስለሌለ ባገኙት አጋጣሚ ለመናገር ይጓጓሉ። ከዓመታት በፊት ያስተዋልኩት አንድ ገጠመኝ መነሻ ላድርግ።

በአንድ መድረክ ላይ አንድ የዕድሜ ባለጸጋ ንግግር እንዲያደርጉ ተጋበዙ። በአዳራሹ የሚበዙት ወጣቶች ናቸው። ወጣቶች ናቸው ማለት እንግዲህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ቀደም ሲል እንዳልኩት አጫጭር ነገሮች የሚወድ ነው። የተጋበዙት አዛውንት ንግግራቸው በጣም ዘለግ አለ። በእያንዳንዱ ወጣት ልብ ውስጥ «አይጨርሱም እንዴ!» የሚል ምኞት ይነበባል። ስልኩን ይነካካል፣ ያፋሽካል፣ ከጎን ያወራል፣ እየወጣ ይሄዳል፤ አዛውንቱ የቀደምት ትዝታቸውን እያወሩ ይህን ትውልድም በነገር ወረፍ ያደርጋሉ።

አዛውንቱ ማሳረጊያ የሚመስል ዓረፍተ ነገር ሲናገሩ አዳራሹ በጭብጨባ ይናጣል፤ የሚያጨበጭቡት በተናገሩት ነገር ተደስተው ሳይሆን «እፎይ ሊጨርሱ ነው» በሚል ደስታ ነው፤ እግረ መንገድም ይበቃዎታል የሚል መልዕክት መሆኑ ነው። አዛውንቱ የሞቀው ጭብጨባ ቀዝቀዝ ሲል ጠብቀው እንደገና አዲስ ታሪክ ይጀምራሉ፤ ታዳሚውም እንደ አዲስ ተስፋ መቁረጥ ይጀምራል። በጭብጨባና በፉጨት አያስቆማቸው ነገር አዛውንት ናቸው፤ በዚህ በኩል ታዳሚው ይመሰገናል። እንዲህ እንዲህ እያለ በብዙ መሰላቸት ሲያልቅ አዳራሹ በጭብጨባ ተናወጠ። ጭብጨባው በአዛውንቱ ንግግር ሳይሆን በመጨረሳቸው (በደስታ) መሆኑን ብዙ ሰው ስላወቀ አፉን ይዞ የሚስቅም ብዙ ነበር።

ይሄ ነገር «ለምን ተፈጠረ?» ብለን ካስተዋልን በሁለት ምክንያት ይሆናል። አንድ በታዳሚው፣ ሁለት ራሳቸው በአዛውንቱ። ታዳሚው ለምን እንዲህ አይነት እውቀት ሰለቸው? አዛውንቱስ የዕድሜ ዘመን ገጠመኛቸው ሁሉ በአንድ መድረክ ያልቅ ይመስል ለምን ነገር ያስረዝማሉ?

መድረክ ላይ አንድ ችግር አለ፤ ጥልቅና ትንታኔ ያላቸው ነገሮች አይወደዱም። የተለመደው አጠር አጠር ያለ የሚያስቅ ነገር ነው። ከዚያ አለፍ ሲልም መንግሥትን ወይም የሆነን አካል የሚሳደብና የሚያስጨበጭብ ነገር ነው። ለነገሩ አሁን አሁን በመድረክ ብቻ ሳይሆን በዋናዎቹ የመገናኛ ብዙኃንም የተለመደው ይሄው ሆኗል። እንዲያውም እኮ መድረክ ሲዘጋጅ ታዳሚን ለማብዛት የሚጠቀሱት ሰዎች አስቂኝ ንግግር ያላቸውን ነው። ጥልቅ ትንታኔ ያላቸው ነገሮች እየጠላን ነው። በዚህ ምክንያት አዘጋጆቹም ሆኑ አቅራቢዎቹ የመድረኩን ዓውድ መለየት አለባቸው። የመድረክ ታዳሚ ሁሉ አጫጭርና አስቂኝ ነገሮች ነው የሚወድ ማለት አይደለም። ለምሳሌ፤ መድረኩ የጥናትና ምርምር መድረክ ከሆነ ታዳሚው የዚያ ዘርፍ ሰው ስለሚሆን አይሰለቸውም። አንዳንድ ጊዜ ግን የተደበላለቀ ነገር ይፈጠራል። ይሄ ማለት ቀለል ያለ መድረክ ላይም የምርምር ሥራ ሊቀርብ ይችላል ማለት ነው።

**እንዲያውም አንድ ሴሳ ገጠመኝ ትዝ አለኝ።**

የጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ፍትሕ መጽሔት ወደ ገበያ ልትገባ በብሔራዊ ቴአትር የተዘጋጀ የምርቃት (ማስተዋወቂያ) የተዘጋጀ መድረክ ነበር። በአዳራሹ መቆሚያ መቀመጫ እስከሚጠፋ ሰው ሞልቷል፤ አብዛኛው ወጣት ነው። ዝግጅቱን አስመልክቶ አዝናኝም አስተማሪም አጫጭር ነገሮች ቀረቡ። ፍትሕ መጽሔት ከዚህ በፊት ፍትህ ጋዜጣ ነበረች። እናም ፍትሕ ጋዜጣን የሚዳስስ ጽሑፍ ሊያቀርብ ብርሃኑ ደቦጭ ተጋበዘ። ገና ሲጀምረው የፍትሕን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ጋዜጦች እያጣቀሰ ጥልቅ ትንታኔ ማቅረብ ጀመረ። በትንታኔው ተመስጬ በጉጉት እያዳመጥኩ ሳለሁ ግን ሊቀጥል አልቻለም። የ«ይበቃሃል» መልዕክት ያለው ጭብጨባ አስተጋባ። ብርሃኑ ወረቀቱን ጠቅልሎ ወረደ። በግሌ በጣም አፈርኩ፤ በጣም ተናደድኩ! ይህኔ እንቶፈንቶ አሉቧልታና ቀልድ ቢያወራ ኖሮ ጭብጨባው የአድናቆት ይሆን ነበር። አሁን ላይ ሳስበው ግን እኔም በከፊል ሳልሳሳት አልቀርም። እኔ የሚዲያ ሰው ስለሆንኩ (ለዚያውም የህትመት ሚዲያ) በሀገራችን የነበረው የህትመት ሚዲያ ታሪክ ሲነገር ተመስጬ ላዳምጥ እችላለሁ። ከሌላ ዘርፍ የመጣ ሰው ግን በእኔ ልክ ሊመሰጥበት አይችልም። እነርሱ የመጡት ፖስተር ላይ የተለጠፉ አንዳንድ ዝነኛ ሰዎችን አይተው ነው።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ለምን ወደ መድረክ እንደሚሄዱ ሁሉ አይታወቅም። ጉዳዩ ስለምን እንደሆነ በግልጽ ተነግሮ እያወቁት ይሄዳሉ። አዳራሹ ውስጥ ሆነው ግን አይከታተሉትም፤ እንዲያውም ሌላም ሰው እንዳይከታተል ነው የሚረብሹት።

ወደ ዕድሜ ባለጸጎች እንመለስ። ከእነዚህ አባቶች የምናገኘው እውቀት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ነው፤ ያ ማለት ተናጋሪው የአይን እማኝ ናቸው ማለት ነው። ያዩትን የኖሩትን ነው የሚነግሩን፤ ዳሩ ግን እንዲህ አይነቶቹን አንሰማም፤ ቆይ ግን እውነት አንወድም ማለት ነው?

በእርጅና ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎችም በባህሪያቸው ነገር ያስረዝማሉ፤ ምክንያቱ ግን ግልጽ ነው። የሚናገሩበት ዕድል ስለሌላቸው ነው። አንተ ወጣቱ በየገባህበትና በየሄድክበት ታወራዋለህ (ወጣት ነህና ብዙ ቦታ ትዞራለህ)፤ አዛውንቱ ግን ብዙ ቦታ አይሄዱም፤ ሲሄዱ ኖረው አሁን ቁጭ ብለው የሚናገሩበት ነበር (ሰሚ ቢገኝ)።

እንዲያውም ልብ ብለን ከሆነ መድረክ ላይ ሲወጡ ብቻ አይደለም ነገር የሚያስረዝሙት። ቀደም ሲል እንዳልኩት የሆነ ነገር ሲያዩ ወይም ሲሰሙ ዝም አይሉም፤ ይናገራሉ። ባያዩና ባይሰሙ ራሱ ዝም ብለው ይናገራሉ። ይመክራሉ፣ ይቆጣሉ፣ ይገስጻሉ።

መድረክ ላይ ሲወጡ ነገር የሚያስረዝሙበት ምክንያት ይሄው ነው፤ የሚናገሩበት ዕድል ስላልነበራቸው ውስጣቸው ያለውን ለመናገር ነው። በነገራችን ላይ አዛውንቶች የአዳራሽ መድረክ ብቻ አይደለም ያጡት፤ መንደር ውስጥ ራሱ የሚያወሩበት ዕድል የለም። ምናልባት የእነርሱ ዕድሜ እኩያ የሆኑ ካላገኙ ወጣቶች ከእነርሱ ጋር አያወሩም። እነርሱ ደግሞ መምከርና መገሰጽ የሚፈልጉት ወጣቱን ነበር እንጂ አዛውንት ከአዛውንትማ ታሪካቸውና ገጠመኛቸው ይመሳሰላል።

እነርሱም እንዲህ የሚያወሩበትና የሚሰማቸው ሲያጡ ውስጣቸው የተጠራቀመውን ብሶት ሁሉ መናገር ይፈልጋሉ።

ምናልባት ግን መድረክ ላይ እንደዚያ በረጅሙ ካልተናገሩ ብሎ መፍረድም ይከብዳል። ምክንያቱም መድረክ ማለት የተወሰነ ሰዓት ያለበት ነው፤ ሌሎች ፕሮግራሞችም የተያዙበት ነው። ይህንን ዓውድ ደግሞ እነርሱ አይረዱም።

ከአባቶች እውቀት እንጠቀም ከተባለ ራሱን የቻለ መድረክ ማዘጋጀት፣ ያ እንኳን ባይቻል ቁጭ ብለን ብናዳምጣቸው፣ የመገናኛ ብዙኃን ዕድል ብንሰጣቸው። ደግሞ እኮ «ተንቀሳቃሽ የቤት መጽሐፍ» እያልን እንጠራቸዋለን፤ ግን አልተጠቀምንባቸውም። የአባቶች እውቀት አይባክን!

# ዓለም አቀፍ



## ቻይና የግመል ትራንስፖርትን ለማሳለጥ የትራፊክ መብራት ተከለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ቻይና የግመል ትራንስፖርትን ለማሳለጥ የትራፊክ መብራት ተከለች።

የዓለማችን ቁጥር ሁለት ልዕለ ሃያል ሀገር የሆነችው ቻይና የግመል ትራንስፖርትን ለማሳለጥ የትራፊክ መብራት ተከላለች።

ሀገሪቱ የግመል ትራንስፖርት መጨናነቅ በሚታይበት ሰሜን ምዕራባዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች ነው የትራፊክ መብራት ተከላ ያከናወነችው።

ጋንሹ ተብሎ የሚጠራው ይህ ግዛት አሸዋማ እና ደረቃማ አካባቢ ሲሆን በዚህ ወቅት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች የሚያዘወትሩት ቦታ ነው።

አካባቢው አሸዋማ በመሆኑ ምክንያትም የግመል ትራንስፖርት ዋነኛ አማራጭ ሲሆን በዚህ ጊዜ የትራንስፖርት መጨናነቅ እንዳይፈጠር ሀገሪቷ የትራፊክ መብራት ተክላለች።

በዚህ አሸዋማ ስፍራ ከ2 ሺህ 400 በላይ ግመሎች ለትራንስፖርት የተዘጋጁ ሲሆን በየዕለቱ በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ጎብኚዎች ወደ ሥፍራው እያቀኑ ነውም ተብሏል።

አሁን ላይ ሚንግሻ ተራራ በየቀኑ በ20 ሺህ እና ከዚያ በላይ ጎብኚዎች እየጎበኙት ነው የተባለ ሲሆን ለግመል ትራንስፖርት አቅራቢ ቻይናውያን ወቅቱ ትልቅ እድል ፈጥሮላቸዋል ተብሏል።

በትራፊክ መብራቱ መሠረትም አረንጓዴ ሲበራ ግመሎቹ የሚጓዙ ሲሆን ቀይ ሲበራ ደግሞ እግረኛ ሰዎች እንዲጓዙ እየተደረገ እንደሚገኝ ተገልጿል።

ቻይናውያን ሀገራቸውን በመጎብኘት ከሌላው ዓለም የተሻለ ልምድ አላቸው የተባለ ሲሆን በዓለም የሠራተኞች ቀን ብቻ 240 ቻይናውያን ወደ ሚንግሻ ተራራ ለጉብኝት አምርተዋል ተብሏል።

በተለይም ሚንግሻ የሚባለውን ተራራ ለመጎብኘት ጎብኚዎች ይህን አሸዋማ ሥፍራ ለማለፍ የግድ ግመልን መጠቀም ግዴታ እንደሆነ ተገልጿል።

## የሩሲያ ጦር በሰሜን ምስራቅ ዩክሬን የሚገኙ አምሥት መንደሮችን ተቆጣጠረ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የሩሲያ ጦር በሰሜን ምስራቅ ዩክሬን ውስጥ በአዲስ መልክ እያረገ ባለው ጥቃት አምስት መንደሮችን መያዙን የሀገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የዩክሬን ባለሥልጣናት በዩክሬን ካርኪቭ ክልል እና ሩሲያ ድንበር ላይ በሚገኙት "ግራጫ ዞን" ውስጥ የሚገኙትን መንደሮች በሩሲያ እጅ ስለመውደቃቸው እስካሁን ያሉት ነገር የለም።

የዩክሬን ጋዜጠኞች እንደዘገቡት ከሆነ ግን ቦሪሲቭካ፣ ኦሂርቴሴቭ፣ ፒሊና እና ስትሪሌቻ የተባሉ መንደሮች ባሳለፍነው አርብ በሩሲያ ወታደሮች እጅ ወድቀዋል።

ሩሲያ የፕሌቴኒቭካ የተባለች መንደርም በጦሯ ቁጥጥር ስር መሆኗን አስታውቃለች።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሊድሚር ዘለንስኪ ከትናንት በስቲያ ምሽት በሰጡት መግለጫ፤ በስትሪሌቻ እና ፕሌቴኒቭካ እንዲሁም በክራስኔ፣ ሞሮኮቬትስ፣ ኦሊኒኮቭ፣ ሉኪንቺ እና ሃቲሽቼ በተባሉ መንደሮች ውስጥ እየተካሄደ ያለው ጦርነት እንደቀጠለ ነው ብለዋል።

"ወታደሮቻችን በጦር ግንባሮቹ የዩክሬናውያንን ድንብር ለማስጠበቅ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ እየወሰዱ ነው" ብለዋል ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ።

እንደ አዲስ ያገረሸውን የሩሲያ ጥቃት ተከትሎ በርካታ ዩክሬናውያን ከመኖሪያቸው ለመልቀቅ መገደዳቸውም ነው የተነገረው።

የዩክሬን ባለሥልጣናት እንደተናገሩት በክልሉ ያገረሸው ጥቃት ከአንድ ሺህ 700 በላይ የዩክሬን ዜጎች በግጭቱ አቅራቢያ ካሉ ሰፈሮች ውስጥ ለቀው ለመውጣት ተገደዋል።

ሩሲያ ከትናንት በስቲያ ቮቭቻንስክ የተባለች መንደርን በአየር እና በሮኬት መደብደቧ የቀጠለች ሲሆን፤ ፖሊሶች እና በጎ ፍቃደኞች ነዋሪዎችን ለማስወጣት ሲሯሯጡ ታይተዋል።

ሩሲያ ካሳለፍነው የካቲት ወር ወዲህ ሩሲያ በዩክሬን ላይ የምትሰነዝረውን ጥቃት አጠናክራ የቀጠለች ሲሆን፤ ዩክሬን በበኩሏ የምእራባውያ የጦር መሣሪያ ድጋፍ በወቅቱ አለመደረሱ ሩሲያ በጦር ግንባር የበላይ እንድትሆን እያደረጋት ነው ብላለች።

የዩክሬን ጦር ዋና አዛዥ ጄነራል አሌክሳንደር ሰርሰይኪ ከሳምንት በፊት በጦር ግንባር ያለው ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱን መግለጻቸው ይታወሳል።

ዩክሬን ቁልፍ ወታደራዊ ሥፍራዎችን ማጣቷን ያመኑት ዋና አዛዡ፤ ሞስኮ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ታክቲካዊ ስኬትን አስመዝግባለች ብለዋል።

ጄነራል አሌክሳንደር ሰርሰይኪ አክለውም ዩክሬን ጦር የሚያስፈልግውን የጦር መሣሪያ ድጋፍ ከአሜሪካ ከማግኘቱ በፊት ሩሲያ ያላትን የወታደርና የጦር መሣሪያ ቁጥር ብላጫ በመጠቀም ቦታዎችን እየተቆጣጠረች መሆኑን አስታውቀዋል።

አሜሪካ ባሳለፍነው ሳምንት ለዩክሬን የ61 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው ወታደራዊ ድጋፍ ለማቅረብ መወሰኗ ይታወቃል።


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የሰሜን ወሎ ዞን ገ/ኢ/ል መምሪያ የግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ር ቡድን በስሩ አገልግሎት ለሚሰጣቸው ለሰሜን ወሎ ዞን እንስሳት ሀብት መምሪያ በጉባላፍቶ ወረዳ ግብርና ግቢ ውስጥ ለሚያሰራው የእንስሳት ክትባት ማከማቻ ዲፖ ሼድ ግንባታና የጥገና አገልግሎት በዋጋ መሙያ ሰንጠረዡ በተመለከተው ዝርዝር መሰረት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል።

**በዚህም መሰረት ተጫራቾች ማሟላት ያለባቸው፡-**

1. በግንባታ ስራ ዘርፍ የተሰማሩና ህጋዊ በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው።
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN NO/ ያላቸው።
3. የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።
4. ደረጃ 9 እና በላይ BC/GC ፍቃድ ያላቸው።
5. ማንኛውም ተጫራቾች ከሞሉት ጠቅላላ ዋጋ ድምር ላይ ብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሺህ ብር ብቻ/ የጨረታ ማስከበሪያ በCPO በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በጥሬ ገንዘብ በመሂ 1 በመ/ቤታችን ገንዘብ ያዥ የተቆረጠ ደረሰኝ እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተሰጠ የጨረታ ማስከበሪያ የዋስትና ደብዳቤ ከጨረታው ኦርጅናል ሰነድ ጋር የተወሰደው የገንዘብ መጠንን በማስጠቀስ በፖስታ ውስጥ አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
6. በተጨማሪም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ ከአደራጁ መስሪያ ቤት ማህበሩ በህጋዊ መንገድ እየሰራ ያለና በጥቃቅንና አነስተኛ አደረጃጀት ውስጥ መኖሩን የሚያስረዳ የድጋፍ ደብደቤ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ የሚችሉ።
7. ጨረታ ላይ የሚሳተፈው ኢንተርፕራይዝ በስሙ የታተመ የሻት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ደረሰኝ ኮፒ በማድረግ ከዋናው ጋር ተገናዝቧል በማለት ከጨረታ ሰነዱ ጋር አብሮ ማቅረብ የሚችል።
8. ተጫራቾች ዋጋ ሲሞሉ ማንኛውንም ግብርና ታክስ አካቶ መሙላት አለባቸው።
9. ተጫራቾች አሸናፊነታቸው ከተገለጸላቸው ባሉት ከ5 የስራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቀርበው ያሸነፉበትን 10% ዋስትና በማስያዝ ውል መፈጸም አለባቸው።
10. የጨረታ ሰነዱ ከ 5/9/2016 እስከ 19/9/ 2016 ዓ.ም ሰሜን ወሎ ዞን ገንዘብ መምሪያ ፋይናንስ ቡድን በመምጣት የጨረታ ሰነድ መውሰድ የምትችሉ ሲሆን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ዋጋ ሞልተው ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
11. ጨረታው በ 20/09/2016 ዓ.ም በ4፡00 ተዘግቶ በዚሁ ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ4፡30 ይከፈታል። በጨረታ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታቸው በሌሉበት የሚከፈት ሆኖ በግዥ መመሪያው ቁጥር 1/2003 መሰረት ተገዥ የመሆን/የመቀበል ግዴታ አለባቸው።
12. ተጫራቾች በሁሉም የጨረታ ሰነዳቸው ላይ ክብ ማህተምና ፊርማ መፈረም ይኖርባቸዋል።
13. ተጫራቾች ዋጋ ሲሞሉ የግንባታ ማቴሪያልን ዋጋ ጨምረው መሙላት ይጠበቅባቸዋል።
14. የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።
15. ውድድሩ በድምር ዋጋ /በሎት/ ስለሆነ ሁሉም ዋጋ መሙያ ሰንጠረዥ መሞላት አለበት።


**ማሳሰቢያ፡-**

* ቲን ነምበር፣ ንግድ ፈቃድ እና የቫት ተመዝጋቢ የምስክር ወረቀት ለየብቻ /ኮንደንስ ሳይደረግ/ ገጽ በገጽ ኮፒ ተደርጎ መያያዝ አለበት።
* መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
* የጨረታ መክፈቻው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በቀጣዩ የስራ ቀን ይከፈታል።

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 0333311597/2680 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**

## የሰሜን ወሎ ዞን ገ/ኢ/ል መምሪያ የግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ር ቡድን

# ስፖርት



## የታዳጊዎቹን የዓለም ዋንጫ ተስፋ የሚወስነው የመልስ ጨዋታ

ብርሃን ፈይሳ

አራት ዙሮች ያሉት የሴቶች ከ17 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ወደ ወሳኙ ምዕራፍ በመሸጋገር ላይ ይገኛል። የዓለም ዋንጫው በዶሚኒካን ሪፐብሊክ አዘጋጅነት በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ መካሄዱን ተከትሎ አፍሪካን በመወከል በመድረኩ ተሳታፊ የሚሆኑ ሀገራት የሚለዩበት ይህ ጨዋታ ሶስተኛ ዙር ላይ ደርሷል። በዚህ ዙር የደርሶ መልስ ጨዋታቸውን ከሚያደርጉት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድንም ከኬንያ አቻው ጋር ከቀናት በኋላ የመልስ ጨዋታውን በማድረግ ቀጣይ እርምጃውን ይለያል።

በአሰልጣኝ ራውዳ አሊ እየተመራ ካለፈው ወር አጋማሽ አንስቶ ዝግጅቱን ሲያደርግ የቆየው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ከኬንያ አቻው ጋር የመጀመሪያ ጨዋታውን በሜዳው ቢያደርግም ውጤት ማስመዝገብ እንዳልቻለ ይታወሳል። ባለፈው ዓርብ የተካሄደው የሁለቱ ቡድኖች ጨዋታ ያለምንም ግብ መጠናቀቁን ተከትሎ በተያዘው ሳምንት መጨረሻ ናይሮቢ ላይ የሚደረገው የመልስ ጨዋታ ለሁለቱም ቡድኖች እጅግ ወሳኝ ነው። አራተኛው ዙር ጨዋታ ከሚቀላቀሉ ስድስት ቡድኖች መካከል የተሻሉት ሶስት ቡድኖች በዓለም ዋንጫው አፍሪካን የሚወክል መሆኑን ተከትሎም ቡድኖቹ ጠንካራ ፍልሚያ እንደሚያደርጉም ይጠበቃል።

በቅርቡ የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድን ዋና አሰልጣኝ በመሆን ከፌዴሬሽኑ ጋር የተፈራረመችው ራውዳ አሊ ቡድኗ የተገኘውን አጋጣሚ መጠቀም እንዳልቻለ ጠቁማለች። የኬንያ ቡድን ዘግቶ ለመጫወት የሞከረ ቢሆንም በኢትዮጵያ በኩል የተገኙትን እድሎች መጠቀም ባለመቻሉ ቡድኖቹ ያለ ግብ ሊለያዩ ችለዋል። ቡድኑ የታዳጊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከመጓጓት ስሜት እንዲሁም የኬንያዊያኑን አጨዋወት ባለመረዳታቸው የተቀናጀ ጨዋታ ማድረግ አልቻሉም ነበር። በእርግጥ ከዚህ ቀደም የኬንያ ብሄራዊ ቡድኑን የአጨዋወት ሁኔታ ለማወቅ አለመቻሉ ለዚህ እንደምክንያት የሚነሳ ሲሆን፤ ከቀናት በፊት የተደረገው ጨዋታ ግን ለመጪው 90 ደቂቃ ጠቃሚ ይሆናል። በመሆኑም ‹‹ግባችንን ሳናስደፍር አጥቅተን በመጫወት ወደ ዓለም ዋንጫው ለማለፍ ጥረት እናደርጋለን›› ስትልም አሰልጣኟ ጠቁማለች።

በማጣሪያው ምድብ ሁለት ከዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ተደልድሎ የነበረው የኬንያ ብሄራዊ ቡድን በጨዋታው እንደማይሳተፍ ባሳወቀው ተጋጣሚው ምክንያት በፎርፌ ወደ ሶስተኛው ዙር ማለፉ የሚታወስ ነው። በአሰልጣኝ ሚልድሬድ ቼቼ የሚመራው ቡድኑ አበበ ቢቂላ ስታዲየም በነበረው ጨዋታ መከላከል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ቢሆንም በመጨረሻው ሰዓት ግን ጫና ለመፍጠር ሞክሮ ነበር። በተያዘው ሳምንት መጨረሻ በሜዳው ላይ የሚያደርገው ጨዋታ ለዓለም ዋንጫው ለማለፍ ወሳኝ እንደመሆኑ ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆን ይታመናል። ይህን ተከትሎም

በዓለም ዋንጫው ከስድስቱ አህጉራት የተወጣጡ 16 ቡድኖች ሲካፈሉ፤ አፍሪካ በሶስት ሀገራት ትወከላለች። ቡድኖቹን ለመለየትም 25 ሀገራት ብሄራዊ ቡድኖቻቸውን ካለፈው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ አንስቶ በማጣሪያው ጨዋታ በማሳተፍ ላይ ይገኛሉ። አራት ዙር ባለው ማጣሪያም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የደቡብ አፍሪካ አቻውን በመርታት ለሶስተኛ ዙር ማለፉ የሚታወስ ነው። ከቀናት በኋላ በሚደረገው የኢትዮጵያ እና ኬንያ በመልስ ጨዋታው አራተኛውን ዙር የሚቀላቀለው ቡድን ከጅቡቲና ብሩንዲ አሸናፊዎች ጋር ይጫወታል። ሁለቱ ቡድኖች ጨዋታቸውን በሶስት ቀናት ልዩነት በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስታዲየም የሚያደርጉ መሆኑ ይታወቃል።



የታዳጊዎቹ ብሔራዊ ቡድን በሳምንቱ መጨረሻ የመልሱን ጨዋታ ናይሮቢ ላይ ያደርጋል፣


## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን ለአዳማ ጋርመንት አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የስሊፒንግ ባግ መስሪያ የፋብሪካ ግብአቶች እና የተለያዩ የአልባሳት መስፊያ ማሽኖች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

ሎት 01 የተለያዩ የስሊፒንግ ባግ መስሪያ የፋብሪካ ግብአቶች፤

ሎት 02፡- የተለያዩ የአልባሳት መስፊያ ማሽኖች

በመሆኑም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶች በጨረታ እንዲሣተፉ ይጋብዛል።

1. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉና በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የግብር ከፋይነትመለያቁጥር/TIN/፣የተጨማሪእሴትታክስምዝገባሠርተፊኬትእናየአምራችነትየምስክርወረቀት (ወኪል ከሆነ ወኪል) መሆናቸው የሚገልፅ ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጨረታሰነዱንአዲስአበባቂርቆስክ/ከተማከሜክሲኮወደቄራበሚወስደውመንገድሳንድማርክሆስፒታል ጎን በሚገኘው በፋውንዴሽኑ ዋና መ/ቤት ኮርፖሬት ግዥ ቡድን በስራ ሰዓት በመቅረብ የማይመለስ ብር 500.00 (አምስት መቶ) በመክፈል ሠነዱን ማግኘት ይችላሉ፡፡ ጨረታው በ16ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዕለቱ 4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በፋውንዴሽኑ የመሰብሰቢያአዳራሽቴክኒካልሰነድይከፈታል፡፡የጨረታፋይናንሻልሰነድየሚከፈትበትወቅትየቴክኒካል ግምገማ እንደተጠናቀቀ በውስጥ ማስታወቂያ (በስልክ ለተጫራቾች) የሚገለጽ ይሆናል።
3. ተጫራቾች የቴክኒከል መጫረቻ ሰነድ አንድ ኦሪጅናል እና አንድ ኮፒ የፋይናንሻልና መጫረቻ ሰነድ አንድ ኦሪጅናል እና አንድ ከፒ ለየብቻ በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
4. ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ጨረታው ከመከፈቱ አስቀድሞ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ማስከበሪያ ዋስትና ለሎት አንድ 200,000 እና ለሎት ሁለት 100,000 በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ /CPO / ወይም በባንክ ጋራንቲ ከጨረታው ቴክኒካል ሰነድ ጋር ማቅረብ አለባቸው።
6. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ።

**አድራሻ፡-**
**መከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን**
**ከቄራ ወደ ሜክሲኮ በሚወስደው መንገድ ሳንድማርክ ሆስፒታል ጎን**
**ስ.ቁጥር 011 557 2734**
**ፓ.ሳ.ቁ.5680 አዲስ አበባ**

**በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን**

## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የኦሮሚያ ደንና ዱር እንሰሳት ድርጅት አርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተለያዩ ብረታ ብረቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም፡-

1. ስለ ጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልፅ የጨረታ ሰነድ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል ዘወትር በስራ ሰዓት አርሲ ነጌሌ ከተማ በሚገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት አርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተገኝተው በመግዛት በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡
2. ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ቀን ተከታታይ ቀናት ክፍት ሆኖ ቆይቶ በ16ኛው ቀን ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት የሚዘጋ ሲሆን በዚህ ቀን ከረፋዱ 4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቅርጫፉ ጽ/ቤት ይከፈታል፡፡ 16 ኛው ቀን እሁድ ወይም በዓል ላይ የሚውል ከሆነ ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ይከፈታል ፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚሆን ከጠቅላላው 5% (አምስት ፐርሰት) የኦሮሚያ ደንና ዱር እንሰሳት ድርጅት አርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስም ሲፒኦ በማሰራት ከጨረታ ሰነዶቻችው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
5. ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 046-116-04-49, 046-116-04-47 ወይም 0913175862 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
6. በዘርፉ ፈቃድ ያላቸውና ተዛማጅነት ያለው በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**በኦሮሚያ ደንና ዱር እንሰሳት ድርጅት የአርሲ ቅ/ጽ/ቤት**